

መዘምራን በጥምቀተ ባሕር በማኅበረ ብዙኃን ላይ እንዳሉ ።

# ማዕዶት ፤



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በጥምቀተ ባሕር ለተሰበሰበው ሕዝብ ክርስቲያን ግሩ ምንዛግ ሲያደርጉ ።

ቍጥር ፩

ኅዳር ፲፱፻፷፱ ዓ/ም/ አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ዕ ዶ ት

ማዕዶት የሚለው ቃል መሠረታዊ አመጣጡ ከልሳነ ግዕዝ ሲሆን ትርጓሜውም ሽግግር ወይም መሸጋገሪያ ማለት ነው ።

ይህ መጽሔት በዚህ ታዳጊ ዓለምና የሽግግር ወቅት ውስጥ በተሐድሶ ላይ የምትገኘውን ጥንታዊቷንና ታሪካዊቷን የኢትዮጵን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ፣ ታሪክና ዜና ጠቅላላ ሕልውናዋንና ወቅታዊ እንቅስቃሴዋን ሁሉ የሚገልጽ ስለሆነ ማዕዶት ተብሎ ተሠየመ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ በስብከትና ማስታወቂያ መምሪያ በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ የሚታተም ፤

አዘጋጅ
ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ

የስልክ ቍጥር 110754

የመልእክት ሣጥን ቍጥር 1283

# ማ ው ጫ ፤

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ፩/ ርእሰ አንቀጽ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | |
| ፪/ የፓ፡ ኤጲስቆጶሳት አመራረጥና በዓለ ሢመት ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ፪ |
| ፫/ የፓ፡ ኤጲስቆጶሳት አጭር የሕይወት ታሪክ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ፮ |
| ፬/ የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልዑካን ጉብኝት በኢትዮጵያ ፡ ፡ | ፲፪ |
| ፭/ ከዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልዑካን የተሰጠ አስተያየት ፡ ፡ ፡ | ፳፮ |
| ፮/ ፓትርያርኩ ለልደት በዓል ያስተላለፉት ቃለ በረከት ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ፳፯ |
| ፯/ የዓለም ሕፃናት አባት ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ፳፰ |
| ፰/ ፓትርያርኩ ስለ ካህናት መደራጀት የሰጡት መግለጫ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ፴፩ |
| ፱/ ስለ መንፈሳዊ ኮሌጅ መሻሻል የተደረገ ውይይት ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ፴፪ |
| ፲/ ስለ ጎንደር ካህናት የርእዮተ ዓለም አመለካከት የተሰጠ ማስገንዘቢያ ፡ ፡ | ፴፬ |
| ፲፩/ የመጀመሪያው ዙር የአፍሪካ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ፴፮ |
| ፲፪/ በዓለ አስተርእዮ (ኤጲፋንያ) ፡ ፡ | ፴፰ |
| ፲፫/ ሥርዓተ ጥምቀት በኢትዮጵያ፡ ፡ ፡ | ፵ |
| ፲፬/ ትምህርተ ሥጋዌ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ ፡ | ፵፪ |

# ርእሰ አንቀጽ

## ጵጵስና ከት/ቤት

ሩስያዊው ሊቀ ጳጳስ አንቶኒ ከጥቂት ዓመታት በፊት የአንድ ከፍተኛ ልዑካን ቡድን መሪ ሆነው ኢትዮጵያን ለመጎብኘት መጥተው ነበር ፤ በጉብኝታቸውም ወቅት ሩስያውያን ካህናት ከኅብረተሰቡ ጋር ስላላቸው ግንዛቤና ቅራኔ ከጋዜጠኞች ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር ታዲያ ሊቀ ጳጳሱ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ «እኛ ሩስያውያን ካህናት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ የምንቀመጠው በቅድሚያ ኅብረተሰቡ የሚያውቀውን ግዙፍ እውቀት ከሞላ ጎደል ካወቅን በኋላ በመሆኑ በተልእኮአችን ሁሉ ምንም ዓይነት ችግር ገጥሞን አያውቅም ይልቁንም ኅብረተሰቡ የሚያውቀውን ግዙፍ እውቀት እኛ እናውቀዋለን ፤ እኛ የምናውቀውን የማይገሠሥ (ረቂቅ)እውቀት ግን ኅብረተሰቡ ስለማያውቀው በኅብረተሰቡ ዘንድ ያለን ከፍተኛ ተወዳጅነትና መከበር እጅግ በጣም የላቀ ነው» በማለትየተናገሩትን መሪና አባታዊ ቃል ለዚህ ሥነ ጽሑፍ መደጎሚያ አድርገን እንድንጠቅሰው የተነሣንበት ዓላማ ያስገድደናል ።

እንደሊቀ ጳጳስ አንቶኒ አባባል በዚህ ግዙፍና ታዳጊ ዓለም ውስጥ የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያን በኃላፊነት ተረክቦ ለመምራት በቅድሚያ የዓለምን ባሕርያዊ ገጽታ መመልከትና ማመዛዘን ብሎም የርእዮታዊውን ትውልድ የልብ ትርታ ጠጋ ብሎ ማዳመጥና ሣይንሣዊ ለሆነው ዕንቆቅልሽ ሁሉ በቂ ፍቺ መስጠት ያስፈልጋል ፤ ቅዱስ መጽሐፍ «በዚህዓለም ሳለህ አስቀድመህ በባላንጋራህ እወቅበት» በማለት የተናገረውም ስለዚህ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው ፤ መንፈሳውያን ሰዎች የማይታየውንና የማይዳሰሰውን ዓለም እንመረምራለን የሚሉት ከሚታየውና ከሚዳሰሰው ዓለም ላይ ቆመው ስለሆነ ፤ የወዲያኛውም ዓለም መቅድሙም ሆነ መርገፉ ይህ ዓለም በመሆኑ የዓለም ብርሃንና የምድር ጨው ተብለው የተሠየሙ ካህናት ሥያሜያቸውን በተግባር ለመግለጽ አስቀድመው የዚህን ዓለም ቋንቋ መረዳትና ከተፈራራቂው ትውልድ ጋር መገናዘብ ይኖርባቸዋል ፤ ለማንኛውም ኪነጥበባትና ቴክኖሎጂያዊ ተግባራት ሁሉ እንግዳ ሆኖ መገኘትም የተልእኮአቸው እንቅፋት መሆኑን ማወቅ አለባቸው ።

ጥንታዊትና የአንድ ሽህ ስድስት መቶ ዓመታት የታሪክ አንጋፋ የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም አንድ ርምጃ ወደፊት ሁለት ርምጃ ወደ ኋላ ስትራመድ የኖረችው የአገልጋዮች ካህናትና የመሪዎችም ጭምር መንፈሳዊ እውቀት ከኅብረተሰቦች እውቀትና ቋንቋ ጋር የተገናዘበ ባለመሆኑ እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ አመለካከቷ በመጥበቡና ተከታዮቿ ምእመናን በስማበለው ሲመሩ በመኖራቸው መሆኑ ግልጽ ነው ፤ «ኢትዮጵያውያን ከምሁራኖቻቸው ጳጳሳትን እንዳይሾሙ» የሚለው የግብጻውያን የተጽዕኖ ቀንበር ከጫንቃዋ ላይ ከወረደላትም ወዲህ ቢሆን ለጵጵስና የሚመረጡት ልጆቿ የሚቀርቡት ከገዳምና ከምናኔ አንዳንድ ጊዜም ከቤተ መንግሥት ስለነበር ገዳማውያኑ በጸሎትና በትህርምት ብቻ በመወሰን ሌሎቹ ደግሞ በዕጨኝነት ያቀረባቸውን ቤተ መንግሥት በማገልገል ስለሚባጁ ለቤተክርስቲያንና ለካህናት እንዲሁም ለምእመናን ሊሰጥ የሚገባው መንፈሳዊ አገልግሎት ተቋርጦ መኖሩ የማይታበል ሐቅ ነው ።

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ አብዮት ከፈነዳና የኅብረተሰብአዊነት አመራር ሥርዓት በመላ ኢትዮጵያ ከተዘረጋ ወዲህ ይህ ሁሉ ጉልታዊ አሠራር በመወገዱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ብሩሕ ተስፋን የተመላና እጅግ በጣም አንፀባራቂ የሆነ የተሐድሶ ገጽታ ይታያል ፤ እነሆ በቤተ መንግሥት ጥቆማና በጥቂት ግለሰቦች አቅራቢነትይፈጸም የነበረው የጵጵስና ምርጫ ተሰርዞ በመላ ኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያንና ካህናት አቅራቢነትና መራጭነት በጠቅላላው ዲሞክራሲያዊ አሠራርን በተመላ ክንውን ትሩፊ ምግባር የሆኑትን አባት ሦስተኛ ፓትርያርክ አድርጋ ሾማለች ፤ በተለይም ባለፈው ዓመት ባካሄደችው የጳጳሳት ምርጫ መነኮሳት ልጆቿን ከብሔር አቀፍና ከዓለም አቀፍ ት/ቤቶች በመሰብሰብ በሙያቸውና በትሩፋታቸው አወዳድራ በአንድ ጊዜ አሥራ ሦስት ምሁራን ጳጳሳትን መርጣ በመሾም በታሪኳ ውስጥ ከፍተኛውን ነጥብ አስፍራለች በአሁኑም ወቅት ረዘም ላለ ጊዜ ብሔር አቀፍና ዓለም አቀፍ ጥናት የወሰዱትን ዶክተሮች ጳጳሳት አድርጋ በመሾም ካለፈው በበለጠ ባሳየችው ለውጥና መሻሻል ያልተገረመ የለም ፣ ይህም አስደናቂና ሌላው አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ነው ።

የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን አበው ግብጽ ወርደው ጵጵስና ተሹመው በመጡበት ወቅት አንድ ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ «እምግብጽ ፀዋዕክዎ ለወልድየ ጵጵስና» ማለትም ጵጵስና ልጄን ከግብጽ ጠራሁት ብሎ በተቀኘው ግሥ ቅኔ ለመረዳት እንደሚቻለው ግብጽ እናገኘው የነበረውን ጵጵስና ኢትዮጵያ ካገኘች ዘመናት አልፈዋል፤ ከገዳማትና ከቤተ መንግሥት አካባቢ ብቻ እናገኘው የነበረውንም ጵጵስና ይኸው ከት/ቤት ማግኘት ጀምረናል ፤ ታላቅ ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን ነው ፤ ወደ ፊትም ቢሆን ጵጵስናን ከት/ቤት ብቻ እንድናገኘው ምኞታችን ነው ፤ ታዲያ የአምናዎቹም ሆኑ የዘንድሮቹ ምሁራን ጳጳሳት በዲግሪያቸውና በዶክትሬታቸው ተመክተው በውዳሴ ከንቱ እንዳይጠለፉ በተቀደሰ ድፍረት እናሳስባቸዋለን፤የሕይወት ታሪካቸውን ብቻ አንብበን እንዳንቀር አባትነታቸውን በተግባር እንጂ በልብሰ ጵጵስና ብቻ እንዳያስመሰክሩ እንማጠናቸዋለን ፤ ጵጵስና ለተፋጠነ ሐዋርያዊ አገልግሎትና ለሃይማኖት ምስክርነት እንጂ ለመከበርና እጅን ለመሳም ብቻ ብሎም ለሥልጣን ሽሚያ አለመሆኑን ተረድተውሠላሳ ዓመት ሙሉ የተኛውን ሲኖዶስ እንዲቀሰቅሱ አደራ እንላቸዋለን ።

www.ethiopianorthodox.org

# የሦስቱ ኤጲስ ቆጶሳት አመራረጥና በዓለ ሢመት

፩/ የታዕካ ነገሥት በዓታ ገዳም አስተዳዳሪ የነበሩት ቆሞስ ሊቀ ሊቃውንት ኤፍሬም ፀዳሉ አቡነ ኤፍሬም ተብለው የአርሲ ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ በመሆን ፤

፲፱፻፸፱ ዓ ም እሑድ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተሾመዋል

የበዓለ ሢመቱ ሥነ ሥርዓት የተከናወነው በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሲሆን በስነ በዓሉ ላይ



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለኤጲስ ቆጶሳቱ የአንበሮተ እዴን ሥርዓተ ጸሎት ባከናወኑበት ወቅት ።

፪/ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ (መጋቤ ካህናት) የነበሩት ቆሞስ ዶክ ተር አባ ጴጥሮስ ኢያሱ ተፈሪ አቡነ ገብርኤል ተብለው መንፈሳዊ ኮሌጅ ኤጲስ ቆጶስ (ዲን) በመሆን !

፫/ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የገዳማት መምሪያ ኃላፊ ነበሩት ዶክተር አባ ሀብተሥላሴ ተስፉ አቡነ ጢሞቴ ዎስ ተብለው በከፋ ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት የጊሚራና ማጂ አውራጃ ኤጲስ ቆጶስ በመሆን ጥር አራት ቀን

ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት፤የመንግሥት ተወካይ፤የቤተ ክህነት ሹማምት ፣ የአድባራት አስተዳዳሪዎችና የገዳማት አበምኔቶች ፤ የወዳጅ አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችና አያሌ ምእመናን ተገኝተዋል ።

ከቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤትስለ በዓለ ሢመቱ በወጣው መርሐ ግብር መሠረት የሥርዓተ ሢመቱና የቅዳሴው ጸሎት በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክና በብፁዐን ሊቃነ



ጳጳሳት ከተከናወነ በኋላ ስነ በዓሉ በዐውደ ምሕረቱ ቀጥሎ ከመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴና ከታዕካ ነገሥት በዓታ የተውጣጡ መዘምራን እንዲሁም የመንፈሳውያን ወጣቶች ዓባላት ልዩ ልዩ ጣዕመ ዝማሬዎችን አሰምተዋል፤ በዓለ

ሁሉ የተስፋ ርምጃ ሲገኝ የቻለው አብዮታዊው መንግሥት በሰጣት ነጻነትና ባስወገደላት ተጽእኖ መሆኑን በማብራራት አስረድተዋል ።

ከዚያም የካህናት ተወካይ ተሿሚዎቹ አባቶች



የኤጲስ ቆጶሳቱ ምርጫ በዲሞክራሲ መንገድ በተፈጸመበት ወቅት ።

ሢመቱን የሚመለከቱ ቅኔዎችም ተበርክተዋል ።

ቀጥሎም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ መርስኤ ኅዘን አበበ ንግግር አድርገዋል ፤ ሥራ አስኪያጁ ባደረጉትም ንግግር የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዘመናት ታሪክ ጠቅሰው በአንድ ዓመት አሥራ ስድስት ኤጲስ ቆጶሳትን መርጣ ስትሾም ድርጊቱ በታሪኳ ውስጥ ከፍተኛ ምዕራፍ የሚሰጠው መሆኑን አመልክተው ብዙ ተከታዮች ያሏት ቤተ ክርስቲያን ወደፊትም ብዙ አባቶች እንደሚያስፈልጓት ገልጸዋል እንዲሁም በአገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከመንፈሳዊ ኮሌጅ ተመርቀው የወጡትን ምሁራን ልጆቿን ጳጳሳት አድርጋ ስትሾም ለቤተ ክርስቲያኒቱ የታሪኳ መጀመሪያ መሆኑን ጠቅሰው ይህ

የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በመዘርዘር ንግግር አድርገዋል ።

በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የተሿሚዎቹን አበው የሕይወት ታሪክና ምግባር ትሩፋት በመጥቀስ እንዲሁም ምእመናንን በመጠበቅና ቤተ ክርስቲያንን በተሐድሶ ጎዳና በማራመድ ረገድ ያለባቸውን ኃላፊነትና ተልእኮ በመግለጽ ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ብርታቱን እንዲሰጣቸው ቡራኬ ከሰጡ በኋላ ጠቅላላ የስነ በዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

ጳጳሳቱ የተመረጡት ከስድስት ዕጩ ቆሞሳት መካከል የትምህርታቸው ፤ የግብረ ገብነታቸውና የቅድስናቸው ከፍተኛነት ተጠንቶ ሲሆን ምርጫውም የተከናወነው ከቅዱስ ሲኖዶስ ዓባላት ፤ ከአድባራት አለቆች ፤ ከካህናት፤



www.ethiopianorthodox.org

ከወጣትና ከሰበካ ጉባኤ መምሪያ የተውጣጡ ፲፱ ተወካ ዮች የሚገኙበት አስመራጭ ኮሚቴ ከተቋቋመ በኋላ ነው ።

በቅዱስ ሲኖዶስ ደንብ መሠረት የጾታ ልዩነት ሳይ ደረግ ምርጫውን ያካሄዱት የሦስቱ ሀገረ ስብከት ተወ ካዮች ማለትም በከፋ ክ/ሀገር ከጊሚራና ማጂ አውራጃ ፤ ከጎንደርና ከአርሲ ክ/ሀገርና ከአዲስ አበባ ከአምስት ዞን ፓትሪያርኩ እንዲፀድቅ አድርጓል ።

በተካሄደው ምርጫ ከፍተኛ ድምጽ በማግኘት በአ ንደኛ ደረጃ የተመረጡት የታእካ ነገሥት በዓታ ገዳም አስተዳዳሪ ቆሞስ ሊቀ ሊቃውንት ኤፍሬም ፀዳሉ ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ የመንፈሳዊ አገል ግሎት መምሪያ ኃላፊ ቆሞስ ዶክተር አባ ጴጥሮስ



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ምርጫውን ባጸደቁበት ወቅት ።

የመጡ ምእመናን፤ወጣትና የካህናት ተወካዮች እንዲሁም የ፲፱ ሀገረ ስብከት ሊቃነ ጳጳሳት ናቸው ።

አስመራጭ ኮሚቴው የምርጫውን ውጤት ካጣራ በኋላ ቃለ ጉባኤ አዘጋጅቶ በመፈራረም ፤ የተመራጮችን የስም ዝርዝር ለቅዱስ ፓትርያርኩ አቅርቦ ምርጫው በቅዱስ ኢያሱ ተፈሪ እንዲሁም በሦስተኛ ደረጃ የገዳማት መምሪያ ኃላፊ በመሆን የሚያገለግሉት ቆሞስ ዶክተር አባ ሀብተ ሥላሴ ተስፋ ናቸው ።

ለተመራጮቹ ቅዳሜ ጥር ፫ ቀን ፹፱ ዓ/ም ከቀኑ በ፲፩ ሰዓት ጸሎተ አስኬማ ተደርጎላቸዋል ።





የበዓለ ሢመቱ ሥርዓተ ጸሎት በተከናወነበት ወቅት ኤጲስ ቆጶሳቱ ቃለ መሐላ ሲፈጽሙ ።



www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለተሿሚዎቹ ኤጲስ ቆጶሳት እርፍ ብርቱን በሰጡበት ወቅት ።



# የ፫ቱ ኤጲስ ቆጶሳት አጭር የሕይወት ታሪክ

## ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም

በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉ ለትና ቡልጋ አውራጃ ደብረ ብርሃን ወረዳ ደነባ ቀበሌ ጥዶ ከሚባለው ሥፍራ በ፲፱፻፳፪ ዓ/ም ግንቦት ፳ ቀን ከአባታቸው ከአቶ ፀዳሉ ገብረ ሐና ፤ ከእናታቸው ከወይዘሮ ሸዋንሰሽ ወልደ ሥላሴ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው ቀበሌ ንባብና ጽሕፈት ዳዊት ሰዓታት ከመሪጌታ ታሪኩ ተማሩ፤ ከዚያም የትምህርት ዓላማቸውን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀጠል መምህር ፍሬ ሰንበት ከሚባሉ ዘንድ ገብተው ጾመ ድጓና የቃል ትምህርት ምዕራፍ ተማሩ ። ከዚያም ኢቲሳ ተክለ ሃይማኖት ገዳም በመሄድ ከታወቁት ሊቀ አፈ መምህር ጌታሁን በኋላ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጢሞቴሬና መዋሥዕት ቅዳሴ በሚገባ ተምረዋል ። ይህንኑ እንደ ፈጸሙ የቅኔንና የግዕዝን ትምህርት ለመማር ከታወቁት ሊቅ ከአለቃ ጥበቡ ገሜ ገብተው ተምረዋል ። ከዚያም ከመምህር በላይ ከሌሎችም መምህራን ዘንድ በመዘዋወር ቅኔውን አስፋፍተዋል ።

ቀጥሎም የመጻሕፍት ትርጓሜን ለመማር ስለ አሰቡ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የመምህራንና ቀሳውስት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ገብተው ሁለት ዓመት በተመላላሽነት በኋላም ሠርከ ኅብስት አግኝተው በአዳሪነት ፣ በሐዲሳት ክፍል በዚያን ጊዜ ሐዲሳት ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ሥምረተ አብ ቀጸላ ዘንድ በመማር በመጻሕ



ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም የአርሲ ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ

ፍት ሐዲሳት ትርጓሜ በመምህርነት ተመርቀው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የስብከት ኮርስ ለብዙ ጊዜያት ተከታትለው በዚሁ የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል።

ምስ ዘንድ እንደገና ፀዋትወ ዜማ ጾመ ድጓ ምዕራፍ አቋቋም ተምረዋል ።

ቀጥሎም ወደ ምድረ ከብድ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም በመሄድ ከመምህር ኪዳነ ማርያም አቋቋም ዝማ



www.ethiopianorthodox.org

በአገልግሎትም በኩል በዚሁ በመታሰቢያ ቤቱ በታዕካ ነገሥት በዓታ ማርያም በሥዕል ቤት ኪዳን ምህረት ቤተ ክርስቲያን ከ፲፱፻፶፩ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፶፮ ዓ/ም ድረስ በመዘምርነት ከ፲፱፻፶፮ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ድረስ በቅዳሴ ተልእኮ ፣ በስብከተ ወንጌል በመምሕርነት ከአሥራ አምስት ዓመታት በላይ አገልግለዋል ።
መዐርገ ምንኩስናን በዚሁ በታዕካ ነገሥት በዓታ ማርያም ገዳም በዚያን ጊዜ ሊቀ ሊቃውንት ኃይለ መስቀል አሁን አቡነ ማቴዎስ የተቀበሉ ሲሆን መዐርገ ቅስና ከአቡነ ማርቆስ የጎጃም ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት በዚሁ በታዕካ ነገሥት በዓታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቀብለዋል ። መዐርገ ቁምስናን በ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን የኤርትራ ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከአቡነ ሚካኤል ተቀብለዋል ።

ከዚያም በ፲፱፻፷፮ ዓ ም በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ የሚገኘው ደብረ በግዕ ገዳም በአስተዳዳሪነትተሰጥቷቸው በቅንነትና በትጋት ከማገልገላቸውም በላይ ፣ በግል ገንዘባቸው ለቤተ ክርስቲያኑ መገልገያ ልብሰ ተክህኖ በመግዛት ፣ ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍት ገዝተው በማበርከትና ዐዲስ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ጉልላቱ ባለመፈጸሙ ይህን ገዝተው በማልበስ ፣ አጥር በማሳጠር በብዙ ሙቶ የሚቈጠር ገንዘብ ከግላቸው አውጥተው በመግዛት ለቤተ ክርስቲያኑ አስፈላጊ የሆኑትን ዕቃዎች ሁሉአሟልተዋል ። ይህ ብቻ ሳይሆን ምዕመናንን በማስተባበር በልዩ ልዩ ቦታዎች አብያተ ክርስቲያናት እንዲሠሩ አድርገዋል ።

ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም በካህናትና በምእመናን ምርጫ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድ ለመታሰቢያ ቤት በዓታ ገዳም ሊቀ ሊቃውንት በመባል ተሹመዋል ።

በገዳሙ ከተሾሙበት ጊዜ አንሥቶ ብዙ የሥራ ፍሬ አሳይተዋል ። ይኸውም ፣ ከባለአደራው ቦርድ ጋር በመነጋገር ቤተ ክርስቲያኗን በማሳደስ አዲስ ደወል በማሠራት ፤ ለካህናቱ የዕደ ጥበብ ሥራ በማቋቋም ፣ የሰበካ ጉባኤው እንዲደራጅና እንዲጠናከር የወጣቶች መንፈሳውያን ማኅበራት የተዋሕዶ እምነትን ጠብቀው እንዲካሄዱ በማድረግ በቅንነትና በትሕትና ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል ላይ ናቸው

# ዶክተር ብፁዕ አቡነ ገብርኤል

ዶክተር ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ከካህን ቤተ ሰብ ማለት ከአባታቸው ከመምህር ገብረ ሕይወትና ከእናታቸው ከወይዘሮ ብርነሽ በ፲፱፻፴፪ ዓ/ም በወሎ ክፍለ ሀገር በዋግ አውራጃ ተወለዱ ፣ የንባብንና የዲቁናን ትምህርት በተወለዱበት ደብር ካከናወኑ በኋላ ማሕጎ ማርያም (ላስታ ) ወደ ተባለ ታላቅ ደብር ተልከው ከፀዋተወ ዜማ ውስጥ ጾመ ድጓንና የዘወትርን ምዕራፍ ከመምህር ኤልሣዕ በሚገባ አጠናቅቀዋል ።

በዚሁ ወቅት በጊዜው የወሎ ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ሢመተ ዲቁናን ተቀብለዋል ። ከዚያም ደብረ ሣሙኤል ከሚባል ታላቅ ደብር የውዳሴ ማርያምንና የቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜ እንዲሁም የዳዊትን ትርጓሜ ከመምህር ጸጋ ዘአብ ወልደ ኢየሱስ ተምረዋል ።

በቅኔ ትምህርት በኩልም ፤

በመጀመሪያ ከመሪጌታ ጥዑመ ልሳን (በዋግ አውራጃ) ቀጥሎም ከመምህር ውቤና ከመምህር መኰንን (ወፍጫት) ተቀኝተዋል ። ቀጥሎም በወሎ ክፍለ ሀገር ከሊቀ ኅሩያን ወልደ ሰንበት የቅኔንና የአገባብን ይትበሀል በሚገባ አጠናቅቀው በመማር በመምህርነት ደረጃ ተመርቀዋል ። እንዲሁምየአቋቋምን ትምህርት በመጠኑ ቀጽለዋል ። ቀጥሎም ወደ አዲስ አበባ መጥተው የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስጳውሎስ መንፈሳዊ ት/ቤት ከመምህር ገብረ ማርያም በየነ ተምረዋል ።

በዘመናዊ ትምህርትም ፤

አንደኛ ደረጃን በኮልፌ ሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ት/ ቤት ፈጽመዋል ። ቀጥሎም ወደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብተው የሁለተኛ ደረጃን ትምህርት ፈጽመዋል ። በዚሁ ወቅት ማለት በ፲፱፻፶፰ ዓ/ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስናን ከቆሞስ ሊቀ ምርፋቅ ኤርምያስ ተቀብለዋል ። በ፲፱፻፶፱ ዓ/ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፈቃድ ከብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሥልጣነ ቅስና ተቀብለዋል ።

በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም ወደ ሶቪዬት ኅብረት ተልከው በሌኒንግራድ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሚሰጠውን የአራት ዓመት ከፍተኛ ትምህርት በከፍተኛ ውጤት በማከናወን ሃይማኖተ አበውን (ፓትሪኦሎጂን) ሜዠር አድርገው በማስተር ኦፍ ዲቪኒቲ ዲግሪ ተመርቀዋል ። ከዚያም በዚሁ መንፈሳዊ ኮሌጅ የዶክትሬት ትምህርታቸውን በሚገባ ፈጽመው በትምህርተ ሥጋዌ (በክርስቶሎጂ) የዶክትሬት ኦፍ ቲኦሎጂድግሪ ተቀብለዋል ።

ቀጥሎም ወደ ሰሜን አሜሪካ ሄደው ከፕሪንቶስን መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ በማስተር ኦፍ ቲኦሎጂዲግሪ ተመርቀዋል ።

በዚሁ ጊዜ በከፍተኛ ውጤት የተቀበሉት የዶክትሬት ድግሪ ሞስኮና ኒዮርክ በሚገኙት በዩኒስኮ የትምህርት ኮሚሽኖች ተመርምሮ ጸድቆላቸዋል ።



በአገልግሎት ረገድም ፣ ወደውጭ አገር ከመሄዳቸው አስቀድሞ በአዲስ አበባ ከተማ በገነተ ጽጌ ቅ/ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሰባኪ ወንጌልነትና በእሁድ ት/ቤት አስተማሪነት ስድስት ዓመት ያህል አገልግለዋል ። እንዲሁም በክረምት ወራት ከውጭ አገር ጥናት (ሪሰርች) ለማድረግ ወደ ኢትዮጵያ በሚመጡበት ወቅት በአዲስ አበባ ደብረ ገሊላ ዐማኑኤል ቤተ ክርስቲያንና በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ት/ቤት ለኮርሰኞች ካህናት ፡ ንፈሳዊ ትምህርት አበርክተዋል ። መምሪያ ኃላፊ ሆነው ሠርተዋል ። ከዚያም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፈቃድ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ዋና ጸሓፊ ሆነው በመሾም በልዩ ልዩ ገዳማት የተለያዩ የልማት ሥራዎችን እንዲከፈቱ አድርገዋል ። እንዲሁም በተለያዩ ክፍላተ ሀገር የካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል ።

ዶክተር ብፁዕ አቡነጴጥሮስ በአሁኑ ወቅት መጋቤ ካህናት ሆነው በመሾም የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ



ዶክተር ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የመንፈሳዊ ኰሌጅ ኤጲስ ቆጶስ ( ዲን )

የተላኩበትንም ትምህርት ፈጽመው ወደ ሀገራቸው ኃላፊ ሆነው ከፍተኛ አገልግሎት በማበርከት ላይ እንደተመለሱ ለተወሰኑ ወራት የትምህርትና የማሠልጠኛ ነበሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ዶክተር ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ

ዶክተር ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ በትግራይ ክፍለ ሀገር በአድዋ አውራጃ በብዜት ወረዳ በፈልፈሉ መድኃኔ ዓለም ቀበሌ በ፲፱፻፴ ዓ/ም ከአባታቸው ከባላም ባራስ ተስፉ ተኰላና ከእናታቸው ከወ ይዘሮ ወለተ ዮሐንስ ኃይሉ ተወለዱ ። ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ የቤተ ክርስቲያን መሠረተ ትም ህርት በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ከአጎ ታቸው ከመ ልአከ ሰላም ገብረ አረጋዊተማሩ ከዚህ በኋላ ትምህ ር ታ ች ው ን ለማስፋፋት ወደ አክሱም ሄደው በአቡነ ጰንጠ ሌዎን ገዳም ከመምህር ገብረ ዮሐንስ ለሙሉ ዲቁና የሚ ያበቃቸውን ትምህርት ተማሩ ፣ ዲቁና ከአቡነ ማርቆስ ተቀበሉ ።

ከዚህ በኋላ ወደ ተወለዱበት አውራጃና ወረዳ (ብዜት) ተመል ሰው ለጥቂት ዓመታት ያህል በፈልፈሉ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን እንዳገለገሉ በአድዋ አውራጃ በአዲአርባቴ ወረዳ ወደ ሚገኘው ደብረ ሃሌ ሉያ አቡነ ሳሙኤል ገዳም ገብተው እየተማሩ በረድእነት ሲያገለ ግሉ ከቆዩ በኋላ በዚሁ ገዳም መነኰሱ ። በዚሁ ገዳም ሳሉ የቅስና ማዕርግ ከብፁዕ አቡነ ማርቆስ የኤ ርትራ ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ተቀበሉ ።

በደብረ ሃሌ ሉያ ገዳም በነበሩበት ጊዜ በልዩ ልዩ ሥራ እየተሠማሩ ብዙ ዓመታት ካገለገሉ በኋላ ዘመ ናዊውን ትምህርት ለመማር በ፲፱፻፶ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጡ ። ቅኔን ማወቅ ለዘመናዊ ትምህርት የሚረዳ መሆኑን በመገንዘብ ወደ ጐጃም ክፍለ ሀገር ሄደው በእ ነማይ አውራጃ በምትገኘው መንግሥቶ ኪዳነ ምሕረት ገብተው ከመምህር (የኔታ) ደጉ ቅኔ ተምረው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ። በጠቅላይ ቤተ ክህነት ተቋ ቁሞ በነበረው የፈታኝ ኮሚቴ ከሌሎች ጋር በመወዳደር በከፍተኛ ውጤት ስላለፉ ሐረር ወደ ሚገኘው መምህ ራን ማሠልጠኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ተልከው በአዳሪነት ገብተው የአንደኛን ደረጃ ትምህርታቸ ውን ጨርሰው በዚሁ አገር በነበሩበት ጊዜ እየተማሩ መደ በኛ አገልግሎታቸው ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክር ስቲያን ሆኖ በየክብረ በዓሉ እዚያው በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ያገለግሉ ነበር ። ይህም ብቻ አይደለም ሐረር በሚገኘው ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ማኅበርም በዓባልነት ገብተው ብዙ አገልግለዋል ።

ከዚህም በኋላ ብሔራዊ ፈተና(ሚኒስትሪ) አልፈው አዲስ አበባ በሚገኘው መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብተው የሁ ለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨረሱ ፣ በዚሁ ትምህ ርት ቤት በነበሩበት ጊዜ በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ያገለግሉነበር ። በመንፈሳዊ ኮሌጅ ወጣቶች ይካ ሄድ በነበረው የስብከተ ወንጌል መንፈሳዊ ማኅበርም ብዙ አገልግለዋል ።

ከዚህ በኋላ የራሽያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለኢ ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የነጻ ትምህርት በሰጠችው መሠረት ለከፍተኛ ትምህርት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሶብዬት ሕብረት ተልከው ለሰባት ዓመታት ያህል ሲማሩ ቆይተው በሌኒንግራድ አካዳሚ ዩኒቨርስቲ ትምህ ርታቸውን አጠናቅቀው ተገቢውን ዲግሪያቸውን በከፍ ተኛ ማዕርግ ተቀብለው ወደአገራቸው ተመልሰዋል ።

### ች ሎ ታ

ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ፣

፩/ ፀዋትወ ዜማ ከመርጌታ ይትባረክ ደብረ ሃሌ ሉያ
፪/ ቅዳሴ ከመምህር ገ/እግዚአብሔር ደብረ ሃሌ ሉያ
፫/ ቅኔ (ከመሪጌታ ደጉ ደብረ መንግሥት ጎጃም

### ዘመናዊ ትምህርት

፩/ የባችለር ዲግሪ
፪/ የማስትሬት ዲግሪ
፫/ የዶክትሬት ዲግሪ

ቋንቋ ፣

፩/ ግዕዝኛ ፣
፪/ ትግሪኛ ከራስ ለሰው የሚተርፍ
፫/ አማርኛ
፬/ እንግሊዝኛ
፭/ ራሽያኛ
፮/ ጀርመንኛ
፯/ ላቲንኛ
፰/ ግሪክኛ ለራስ ብቻ
፱/ ዕብራይስጥኛ

ማዕርግ ፣

፩/ ዲቁና
፪/ ምንኩስና
፫/ ቅስና

አገልግሎት ከዘመናዊ ትምህርት በፊት በትግራይ ክፍለ ሀገር ደብረ ሃሌ ሉያ ገዳም

፩/ በረድእነት
፪/ በመጋቢነት
፫/ በአስተዳዳሪነት (በመምህርነት አይደለም ።)

ከዘመናዊ ትምህርት በኋላ በአዲስ አበባ ፤



፩/ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ቤት በድሬክተርነት
፪/ በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ በአስተዳዳሪነት ( ሊቀ ሥልጣናት)
፫/ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የዓለም አብያተ ክርስቲያ ናት የውጭ ግን ኙነት ጉዳይ ኃላፊ
፬/ አሁን የገዳማት መምሪያ ኃላፊ የኢትዮጵያ ኦርቶ

፫/ በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም የመላ አፍሪካ አብያተ ክርስቲያና ት ቶጎ ሎሚ
፬/ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም የወጣቶች የክርስቲያን ጉባኤ ሶብ የት ኅብረት
፭/ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የመላ አፍሪቃ የክርስቲያን የሰላም ጉባኤፍሪታወን ፣
፮/ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም የመላ አፍሪቃ አብያተ ክር ስቲ ያናት በጋናሆ



ዶክተር ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የጊሚራና የማጂ አውራጃዎች ኤጲስቆጶስ

ዶክስ ቤተ ክርስ ቲያንን በመወከል በየጊዜው ዓለም አቀፋዊ መልእክተኛነት ፣

እንደ አውሮጳ ዘመን አቆጣጠር ፣

፩/ በሰኔ ወር ፲፱፻፷፱ ዓ/ም የመላ አፍሪካ አብያተ ክርስ ቲያናት በካሜሮን ያውንዴ

፪/ በግንቦት ወር ፲፱፻፷፱ ዓ/ም የዓለም የገዳማት ጉባኤ በግብፅ ካይሮ

፯/ በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም አምስተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲ ያናት ጉባኤ ናይሮቢ ፤

፰/ በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም የመላ አፍሪቃ አብያተ ክርስቲያ ናት ዛምቢያ ሉሳካ ፣

፱/ በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም የወጣቶች የክርስቲያን የሰላም ጉባኤ ሶፊያ ፲/ በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም የክርስቲያን የሰላም ጉባኤ ፕራግ ፣ ተሳትፈዋል



www.ethiopianorthodox.org

# የዓለም ክ/ የሰላም ጉባኤ ከፍተኛ ልዑካን ጉብኝት በኢትዮጵያ

፩/ የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ከፍተኛች መል እክተኞች

ሀ/ ጳጳስ ዶክተር ካሮሊ ቶት የዓለም ክርስቲያኖች የሰ ላም ጉባኤ ዋና ፕሬዚዳንት የቡድኑ መሪ

ለ/ ብፁዕ ፍላሬት በሶብየት ኅብረት የጋሊሲያና

ምክር ቤት ዋና ጸሓፊና የአፍሪካ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ዋና ጸሓፊ ፤

ረ/ ካህን ላዛሩስ ከፈረንሳይ በሕመም ምክንያት አልመጡም ። ነገር ግን በርሳቸው ሥፍራ ሚስተር ሰርጌይ የመትሮፖሊት ፊላሬት አስተርጓሚ በመሆን



የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ከፍተኛ ልዑካን አዲስ አበባ በገቡበት ወቅት

የመላዋ ኡክራይን መትሮፖሊት የዓለም ክርስ ቲያኖች የሰላም ጉባኤ የኮንቲኒዩሺን ኮሚቴ ሊቀመንበር (ከሶብየት ኅብረት)

ሐ/ ሬቨረንድ ክርሲቲ ሮዛ የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ም/ዋና ጸሓፊና የእስያ ክርስቲያ ኖች የሰላም ጉባኤ ዋና ጸሓፊ ፤ (ከሲሪላንካ)

መ/ ካኖን ኢ. ራይት የሰላም ጉባኤው ዓባል (ከእን ግሊዝ)

ሠ/ ሬቨረንድ ሻውሪ የታንዛኒያ አብያተ ክርስቲያን

ተገኝተዋል ።

፪/ የሰላም ልኡካኑ ኅዳር ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ረቡዕ በአምስት ሰዓት አዲስ አበባ ዓለም አቀፍ አየር ማረ ፊያ ቦሌ ሲደርሱ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፣ የቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅና ሹማምንት የልማት ኮሚሽን ዋና ጸሓፊና የመምሪያው ኃላፊዎች

የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳውያን



ማኅበራት ወጣቶች ፤ በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለ ያየንም ኮሚቴ ዓባላት ፤ ጓድ የመቶ አለቃ ጥበቡ ሽፈ ራው የኢትዮጵያ የትግል ፤ የሰላምና የወዳጅነት ኮሚቴ ዋና ጸሓፊና አቶ ኢያሱ በዕደ ማርያም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፕሮቶኮል ሹም የደመቀና ታላቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ለስድስቱም ልኡካን ወጣቶች ዕቅፍ አበባ አበርክተዋል ።

ኢትዮጵያ ቅድመ አብዮት የነበረችበትን ፤ ሰፊው ሕዝቧ በጥቂት ፊውዳሎች ሲረገጥ ፤ ሲበዘበዝ እንደነበረና ድኅረ አብዮት ፊውዳላዊው የዘውድ መንግሥት ተወግዶ የእኩ ልነት ፣ የትክክለኛ ፍትሕ ፣ የነጻነትና የሰላም ኑሮን ለመ ኖር ሲታገል የውስጥና የውጭ ጠላቶች ተነሥተው በምሥ ራቅና በደቡብ እንዲሁም በሰሜን ኢትዮጵያ የተከፈለውን መሥዋዕትነትና ድል በኋላም በአረንጓዴው ዘመቻ ሰፊው



ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ከፍተኛ ልዑካንን ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት ።

፫/ መንግሥታችን ለሰላም ልኡካን ጉብኝት ከፍተኛ ግምት ሰጥቶ በቤተ መንግሥት የእንግዶች ማረፊያ እንዲያርፉ ስለፈቀደ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በክብር ታጅበው ወደማረፊያቸው በመሄድ ዐርፈዋል ።

፬/በመጡበት ዕለት ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለማር ያም የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስ ተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር ፤ የምኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የአብዮታዊው ጦር ጠቅላይ አዛዥ ለእንግዶቹ ሰፊ ጊዜ ሰጥተው ስላነጋገሩአቸው ኅብረተ ሰብአዊት

የኢትዮጵያ ሕዝብ ድንቁርናን ፤ በሽታን ፤ ድኅነትን ለማውደም አብዮታዊው መንግሥት በአወጣለት መርሐ ግብር የተያያዘውን ሐቀኛ ትግል አንድ በአንድ ተንትነው አስረድተዋቸዋል ።

የሰላም ልዑካኑ በጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ገለጻ እጅግ በጣም ረክተዋል ። ውይይ ቱም ተፈጽሞ ከወጡ በኋላ «ጸጥ ያለ በእውነት የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅር የተቀረጸበት አስተዋይ መሪ» እያሉ ርስ በርሳቸው በአድናቆት ሲወያዩ ሰንብተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

በዚሁ ዕለት ማታ በማዘጋጃቤቱ በንድ ዶክተር ዓለሙ አበበ የአዲስ አበባ ከተማ አጠቃላይ ምክር ቤት የተ ደረገላቸው ገለጻ ተጨባጩን የኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ፣ ይዘትና ውጤት እንዲረዱት ረድቷቸዋል ። በአዳራሹ የተደረደረውን ለአብዮታቸውና ለሰፊው ሕዝባቸው መሥዋዕት የሆኑትን አብዮታውያን ሥዕለ ገጽ በተመለከቱ ጊዜ አብዮቱ አሁን ከደረሰበት ሰላ ማዊ ደረጃ ለመድረስ የተከፈለውን መሥዋዕትነት እንዲመዝኑት የኢምፔሪያሊስትን ተንኮል እንዲረዱት ረድቷቸዋል ።

፫ በመጡበት ዕለት ማታ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ታላቅ የራት ግብዣ አድርገውላቸዋል ። በራት ግብረዱ ሆኗል ። ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩና ከቅዱስ ሲኖዶስ ዓባላት ጋር በማግስቱ እንደገና የመወያየት ዕድል ገጥሟቸው ስለነበር ኢምፔሪያሊስቶችና ሌሎችም የአገራችን እድገት ጠላቶች በሃይማኖት ተጠግተው የሚያስወሩት ወሬ ትክክል አለመሆኑን የሰላም ልኡካኑ እንዲገነዘቡት ተደርጓል ። በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ በቤተ ክርስቲያናችንና በዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ መካከል ወዳጅነት እንዲጠነክር በውይይቱ ወቅት ተስማምተዋል ።

፭/ ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ጧት የመንበረ መንግሥት ገብርኤልንና የበአታን አብያተ ክርስቲያን ጎብኝተዋል ። ብፁዕ አቡነ ጎርጎሬዎስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ የሁለቱም አብያተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች የሰበካ ጉባኤ ዓባላት ፤




የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልኡካን በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ተገኝተው ውይይት ባደረጉበት ወቅት ።

ዣውም ወቅት በተደረገው የወዳጅነት የንግግር ለውጥ በኅብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ የሃይማኖት እኩልነት መሰጠቱንና ይህም በተግባር እየታየ መሆኑን እንዲ መዘምራን ፣ ከአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያን የተውጣጡ ወጣቶች በመዝሙርና በይባቤ ተቀብለዋቸዋል ። ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ እንግዶቹን ከምእመናን



ጋር አስተዋውቀዋል ። የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባ ኤን ዓላማም ለምእመናን ገልጸዋል ።

ከቀኑ ስምንት ሰዓት ተኩል ጀምሮ በብሔራዊ ትያ ትር አዳራሽ በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም ኮሚቴ ጥሪ ያደረገላቸው የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታ ተከታዮች ግንባር ፈጥረው ለወያፊቱ ከአብዮታዊው መን ግሥት ጋር ሰፊውንና ጭቁኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ መር ዳት እንዳለባቸው በማያወላውል ሁኔታ ነግረዋቸዋል ። የኦርቶዶክስና የባብቲስት እምነት ተከታይ ክርስቲያን ወጣቶች መንፈሳዊ መዝሙር ዘምረውላቸዋል ። ኦርቶ



የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ፕሬዚዳንት አቡነ ዶክተር ካሮሊቶስ በብሔራዊ ቲያትር አዳራሽ ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር ሲያደርጉ ።


ታዮች ፣ በኢትዮጵያ የትግል ፣ የሰላምና ወዳጅነት ኮሚቴ ጽ/ቤት በኩል የተጠሩ የሕዝባውያን ድርጅቶች ዓባላት በተገኙበት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ውይይት ተደርጓል ። የእስልምና እምነት ተከታዮች ተጠሪዎች በእናት አገር ፍቅር ተመስጠው ፤ የውስጥና የውጭ ጠላት በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈጸመውን ደባ አጋልጠው ፤ ቅድመ አብዮት የሃይማኖት እኩልነት አለመኖሩን ፣ ድኅረ አብዮት ያገኙትን የሃይማኖት እኩልነት አውስተው አመስግነው ተናግረዋል ፤ የሰላም ልኡካኑም የኢትዮጵያ አብዮት ለእኩልነት ፤ ለትክክለኛ ፍትሕ ፤ ለሰላምና ለኢኮኖሚ ነጻነት የተከሠተ መሆኑን ማረጋገጣቸውን በታላቅ ደስታ ገልጸዋል ። ልዩ ልዩ የሃይማኖት ድርጅቶችና ዶክሳውያን ወጣቶች የቤተ ክርስቲያንና የአገሪቱ ታላቅ ቅርስ የሆነውን የያሬድን ዜማ በክብርና በጸናጽል እየታጀቡ አሰምተዋቸዋል ። በዚህም የእንግዶቹ ልቡናና አእምሮ ረክቷል ። በዚሁ ዕለት ማታ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በግዮን ሆቴል የራት ግብዣ አድርጎላቸዋል ። ስጦታም አበርክቷል ።

፱/ ኅዳር ፰ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ዓርብ ከጧቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል በመንግሥታችን ትእዛዝ በተዘጋጀው በኢትዮጵያ አርሚ አቢየሽን ሄልኮፕተር በዝዋይ ወደሚገኘው የሕጻናት አምባ ተጉዘዋል በዚያም ፣ሠ ተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ ሻለቃ የአምባው ዋና አስተዳዳሪ ሻለቃ እስጢፋኖ



www.ethiopianorthodox.org

የሐይቆችና ቡታጅራ አውራጃ አስተዳዳሪ ሻለቃ አሸብር በጠቅላላው የአምባው ሠራተኞችና ወጣቶች ተሰልፈው የሞቀና የደመቀ ወግ አደራዊ ስነ ሥርዓት የተመላበት አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ሻለቃ መሐሪና የሥራው አስፈጻሚ ሻለቃ እስጢፋኖስ በቀለጠፈና ደስ በሚያሰኝ ቃል ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ለአገራቸው ክብርና ነጻነት ፤ ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እድገት ከውስጥና ከውጭ ጠላት ጋር በመዋደቅ ሕይወታቸውን የሠውት ጀግኖች ልጆች የሙታን ልጆችሆነውእንዳይቀሩና የትም ባክነው ለማኞች እንዳይሆኑ በማሰብ ወሮታም ለመ ክፈል ይህን ታላቅ አምባ እንዲሠራ አዝዞ በተለይም ትክክል መሆኑን ይህም አብዮታዊ ርምጃ ለእኩልነት ፤ ለትክክለኛ ፍትሕ ፣ ለነጻነትና ሰላም መሆኑን መረዳ ታቸውን ገልጸዋል ። በፍጻሜውም ሻለቃ መሐሪ በአም ባው ሠራተኞች ስም ስጦታ አበርክተው የቀዝቃዛ መጠጥ ግብዣ ተደርጎላቸው ጉዞው በዙዋይ ከተማ አቅራቢያ ወደሚገኘው የካህናት ማሠልጠኛና ባሕታውያን ወደሠ ፈሩበት ሥፍራ አምርቷል ። በዚህም ጓድ የአውራጃው አስተዳዳሪ ፣ የአውራጃው ዋና ጸሓፊ ፣ የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ የልዩ ልዩ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣኖች ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት ፣ የማሠልጠኛው ካህናትና ወጣ ቶች ተሰልፈው የደመቀ አቀባበል አድርገውላቸዋል ዕቅፍ




የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልዑካን የሕፃናትን አምባ በጐበኙበት ወቅት ።

ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ከዚህ ባለመ ለየት ጥብቅ ቊጥጥር እያደረጉ በስምንት ወርሥራ የሕጻናቱ አምባ አሁን የደረሰበትን ደረጃና የወደፊት ዕቅድ ተንትነው በየፈረቃ አስረድተዋል ፣ እየተዘዋወሩ እንዲጎበኙም አድ ርገዋል ። በመጨረሻም እንግዶቹ በየተራ የሠራተኞቹን ሞራል የሚያበረታ ፤ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ርምጃ አበባም ተበርክቶላቸዋል። ባሕታውያን መነኮሳትና የማሠ ልጠኛው ካህናት በመተባበር ያለሙትን ልማት እየተዘዋ ወሩ ጎብኝተዋል ። የዙሪያው ሕዝብ ወጣቶችና ካህናት በተሰበሰቡበት የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጎር ጎርዮስ በኢትዮጵያ ያለውን የሃይማኖት እኩልነት ፣ አብ ዮቱ ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስገኘውን ድልና ዕድል ፤



የኢምፔሪያሊስቶችን ሴራና ተንኮል በማጋለጥ ንግግር አድርገዋል ። የሰላም ልኡካኑም በተመለከቱት ሁሉ መደ ሰታቸውን ካህናቱም የጀመሩትን የልማት ሥራ ከግቡ እንዲያደርሱ የማጽናኛ ቃል ተናግረዋል ።

፰/ ጉዞው ያመራው ከዝዋይ ወደ ወንጂ ኩሪፍቱ ነበር የአብዮቱን አጀማመር ፤ በአድኃሪው የሶማሌ ጦር ፤ ከሰ ሜን ተገንጣይ ወንበዴዎች ጋር የተደረገውን ጦርነትና የተገኘውን ድል ፣ የአረንጓዴውን ዘመቻ ኺደት የሚያመለ ክተውን ታላቅ ፊልም አሳይተዋቸዋል ። ይህም ለሰላም ልኡካኑ ታሪኩንና የአብዮቱን ሐቅ እንዲረዱ ረድቷል ።



የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልዑካን የዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ ት/ ቤትንና የልማቱን ሥራ በጐበኙበት ወቅት

በሄሊኮፕተር የዙዋይን ሐይቅና ደሴቶችን እየተመለከቱ ኢትዮጵያ የለበሰችውን የተፈጥሮ ጸጋ ከማድነቃቸውም በላይ በተለይም ወንጂ የለበሰው አረንጓዴ ልቡናቸው በደስታ እንዲሞላ አድርጎታል ።

በፍጻሜውም በአዳማ ሆቴል አጠገብ በማረፍ የምሳ ግብዣ ተደርጎላቸዋል ።

በዚህም ወቅት የቤተ ክህነት ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ መርስኤ ኀዘን አበበ ከቤተ ክህነትና ከልማት ኮሚሽን የንብረትና የገንዘብ ኃላፊዎች ጋር በመ ገኘት ተቀብለዋቸዋል ። ከምሳ ግብዣው በኋላ ወደ ማረ ፊያቸው ተመልሰዋል ።

በዚህ ዕለት ማታ ጓድ የመቶ አለቃ ተሾመ ቅድመ አብዮት በመቅደላ ፤ በአድዋና በማይጨው ኤምፔሪያ ሊስቶች በኢትዮጵያ ላይ ከፍተውት የነበረውን ጦርነት ፤

፱/ ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም

ሀ/ ከጧቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ጀምሮ በከፍተኛ ፩—0 ፰ ቀበሌን የሥራ ርምጃ በከተማ ነዋሪዎች አጠቃላይ ማኅበር ምክር ቤት ዓባልና በቀበሌው ሊቀ መንበር አማ ካይነት የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሹን ፤ የሕጻናት መዋ ዕልን ፣ ቤተ መጻሕፍቱንና ሕዝቡ ዕረፍት የሚያደርግ በትን ሥፍራ በመዘዋወር ጎብኝተዋል ። የቀበሌው ሊቀ መንበር ከዚህ ደረጃ ለመድረስ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈለውን መሥዋዕት ነት አብራርተዋል ።

ለ/ በየካቲት ፲፪ አደባባይ አጠገብ የሚገኙ የኢትዮ ጵያን አናብስት (አንበሶችን) ጎብኝተዋል ።

፲/ በድኩማን የሚሠራውን የተሕዋዶ ጥበብ የጃንጥላና የባትሪ ፋብሪካ ጎብኝተዋል ፤ ከዚያ ሲደርሱ የንግድ ሚኒ ስቴር ቋሚ ተጠሪ ጓድ ማሞና የፋብሪካው ሥራ አስኪያጅ



www.ethiopianorthodox.org

ሌሎችም ባለሥልጣኖች በክብር ተቀብለዋቸዋል ። ድኩ
ማኑ ማለትም ዓይነ ዕ■ራንና አካለ ስንኩላን የፋብሪካውን
ሥራ በቀለጠፈ ሁኔታ ሲያንቀሳቅሱ እየተዘዋወሩ ጎብ
ኝተዋል ። የኢትዮጵያ አብዮት አካለ ስንኩላንና ዓይነ
ዕውራን በየመንገዱና በየአብያተ ክርስቲያኑ በመለመን
ፈንታ በዚህ ዓይነት እየሠሩ ራሳቸውን ችለው እንዲተዳደሩ
መርሐ ግብር እየቀየሰ መሆኑ በአስጎብኝዎቹ ተገልጾላቸ
ዋል ። በጉብኝቱ ፍጻሜ የድኩማኑ የሥራ ውጤት የሆነ
ስጦታ ተበርክቶላቸው በጉብኝቱም መደሰታቸውን ገል
ጸዋል ።

፲፩/ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሥር የሚካሄ
በመነኮሳቱ የተሠራ ዕፀ መስቀል አበርክተውላቸዋል ።
የሰላም ልኡካኑ በኢትዮጵያዊው መነኩሴ የተሠራው
በጠረጴዛ ላይ የሚቀመጥ ዕፀ መስቀል በጣም ስላስደሰ
ታቸው ገዝተው ለእንግሊዝ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ
በዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ስም ስጦታ ልከዋል ።
፲፪/ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን ጉዞው ወደ ደብረ ዘይት
ሆኗል ። ሰባት ሰዓት ሲሆን በደብረ ዘይት ሆራ ሆቴል
ዕረፍት እንዲያደርጉ ተደርጓል ። የሆራ ሆቴል ቅድመ
አብዮት ራስ ሆቴል በመባል የታወቀ ሲሆን ይንደላቀቁ
በት የነበሩት ጥቂቶች ባለጊዜዎች ማለትም የመሳፍንት
ሐረጎች ብቻ መሆናቸውንና ድኅረ አብዮት ግን ማንኛውም
ጭቁን ሠራተኛ እየመጣ እንደየችሎታው ዕረፍት ሊያ



የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልዑካን በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው መግለጫ በሰጡበት ወቅት

ደውን የጎፋ ገብርኤል ዕደ ጥበብ የካህናት ማሰልጠኛ
ትምህርት ቤትን ጎብኝተዋል ። መነኮሳት በሽማ ፣ በብረታ
ብረትና በአናጢነት መሰልጠን ሙያ ተሰማርተው ሲሠሩ
በማየታቸው በሠርቶ ማሳያው የተገኘውንም የምርት
ውጤት በመመልከታቸው ልቦናቸው በደስታ መመላቱን
ገልጸዋል ። የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ጓድ ብርሃኑ ቸኮል
ደርግበት የሚችልበት እንዲሆን መደረጉ ተገልጾላቸዋል ።
በዚያም አቶ መርስዔ ሐዘን አበበና ሌሎችም የቤተ ክህ
ነት ባለሥልጣኖች ተገኝተው በባሕሩ አንጻር በፎቁ ላይ
ታላቅ የምሳ ግብዣ ተደርጎላቸዋል ። በምሳው ግብዣ
ወቅት እንደተመለከቱትየተደረገላቸውን አቀባበልና በአእ
ምሮአቸው የተቀረጸውን የሰፊውን የኢትዮጵያን ሕዝብ



ፍቅር እያወሱ ደስ የሚያሰኝ ጊዜ አሳልፈዋል ።
፲፫/ ከምሳው ግብዣ በኋላ ወደጀግኖች አምባ አምርተ
ዋል ። በዚያም የጀግኖች አምባ አስተዳዳሪ ኮሎኔል ሞላ
ልኝ በላይ ፣ ጀግኖችና ሠራተኞች የደመቀ አቀባበል አደ
ርገውላቸዋል ። የጀግኖቹ አምባ አስተዳዳሪ በጓድ ሊቀ
መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የተለየ ትኩረትና
ትጋት በአብዮታውያን ጓዶቻቸው ተባባሪነት ደማቸውን
ላፈሰሱ ፣ አጥንታቸውን ለከሰከሱ፣ የአካል ጉድለት ለደረ
ሰባቸው ጀግኖች መንከባከቢያና መማሪያ ፣ ከኅብ
ረተሰቡ ተቀላቅለው እንዲሠሩ ለማድረግ ማዘጋጃ እን
ዲሆን አምባቸው መሠራቱን በዝርዝር አስረድተዋቸ
ዋል ። ክፍሎቹንም እየተዘዋወሩ ጎብኝተዋል ፣ በሆስፒ
ታሉ ውስጥ ተገኝተው በመታከም ላይ ያሉትንም ጀግ
ኖች ጎብኝተው አጽናንተዋቸዋል ።
ማሌያ መንግሥት ከኤምፔሪያሊስቶች ጋር ተመሣጥሮ
በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰው ጉዳት ያሳዘናቸው መሆኑንና
በተገኘውም ሐቀኛ ድል መደሰታቸውን የሰላም ልኡካን
መሪ ጳጳስ ዶክተር ካሮሊ ቶት ገልጸውላቸዋል ።

መትሮ—ፖሊት ብፁዕ ፍላሬት በበኩላቸው በአገ
ራቸው ሩሲያ ኅብረተሰብአዊነት በታላቅ ትግል እንደ
ተመሠረተና ተከፍሎ የነበረው መሥዋዕትነት ከፍተኛ
መሆኑን ለጀግኖቹ ገልጸዋል ። በተለይም በኅብረተ ሰብአ
ዊነት ራሳችንን ለመቻል ጥረት ስናደርግ የሂትለር ጦር
ወርሮን ስንዋደቅ «አንድ ጀግና ፓይለት ሁለት እግሮቹን
አጣ ፣ እግሮቹ ቢቆረጡም የጀግንነት ልቡ ስላልተቆረጠ
እንደገና ወደጦር ሜዳ ለመሄድ የጀግንነት ወኔው ይታገ
ለው ጀመር ፤ ሰው ሠራሽ እግሮች ገቡለት ከዚያ በኋላ
ወደአኤሮፕላኔ ውስዱኝና በሰው ሠራሽ እግሮቼ እንዴት


በመጨረሻም ጀግኖቹ ተሰልፈው ወደሚገኙበት መድ
ረክ ሄደው በተመለከቱት ፤ አብዮታዊው መንግሥት ለእ
ናት አገራቸው አካላቸውን ለገበሩት ጀግኖች አምባውንና
የመማሪያ ስፍራዎችን በማዘጋጀቱና ጀግኖችን በመንከ
ባከቡ በደስታ ልባቸው የተነካ መሆኑን ፣ አድኃሪው የሶ
እንደማበር ላጥና ብሎ አስቸገረ እንደገና ከተለማመደ በኋላ
የጦር አኤሮፕላኑን እያበረረ የአገሩን ጠላቶች ማውደም
ቀጠለ ፣ ይህ ጀግና ታላቅ የታሪክ መጽሐፍ ታትሞለት
የዓለም ሕዝብ እያነበበው ነው ። እናንተም አካላችሁ ቢጎ
ድል ለእናት አገራችሁና ለሰፊው ሕዝባችሁ የከፈላችሁት



www.ethiopianorthodox.org

ሕይወት ነውና አካላችን ኅደለ ብላችሁ ቅር ልትሰኙ አይ ገባም ፣ በጣም ደስ ይበላችሁ ። አገራችሁና አብዮታዊው መንግሥት ወርታችሁን እየከፈላችሁ ናችሁ ፤ በተለይም በታሪክ ምዕራፍ ከፍተኛውን ሥፍራ ይዛችኋል በማለት ሞራላቸውን የሚያዳብር ንግግር አድርገውላቸዋል ። በዚህም የጉብኝቱ ፍጻሜ ሆኖ ወደ አዲስ አበባ ተመል ሰዋል ።

ደረጉት ጉብኝትና በየደረሱበት በተደረገላቸው ሐቀኛ ገለጻ በጣም የተደሰቱ መሆናቸውን ለጓድ ሻምበል ገሰሰ ወልደ ኪዳን በታላቅ ደስታ ገልጸውላቸዋል ። በዚሁ ዕለት ማታ በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለያየንም ኮሚቴ በራስ ሆቴል ታላቅ የራት ግብዣ አድርጎላቸዋል ። በግብዣውም ወቅት የኮሚቴው ሊቀመንበር ሊቀካህናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ ፣ ሐጅ አህመድ ሻፊ የኮሚቴው ዓባል



የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ካህናት የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልኡካንን በሽብሸባ በተቀበሉበት ወቅት

ኅዳር ፳፩ ቀን ማታ ጓድ ሻምበል ገሰሰ ወልደ ኪዳን የደርጉ ቋሚ ኮሚቴ ዓባልና የማኅበራዊ ጉዳይ ኃላፊ ወደ እንግዶቹ ማረፊያ መጥተው አነጋግረዋቸዋል ። ጓድ ሻም በል ገሰሰ «አብዮታችን ከሃይማኖትና ከሃይማኖት ድር ጅቶች ጋር ጸብአ የለውም ፣ ጸቡ ከድኅነት ፣ ከድንቁርና ፣ ከበሽታ ፣ ከኢምፔሪያሊስት ተጽዕኖና ብዝበዛ ጋር ነው ። የሃይማኖትን ካባ ለብሶ የኢምፔሪያሊስቶችና የአብዮት ቀልባሾች መልእክተኛ ከሚሆነው ጋር ብቻ ነው ። ሁላች ንም አብዮታውያን የቆምነው ለሰላምና ለነጻነት ነው» በማለት አንድ በአንድ በመተንተን አስረድተዋቸዋል ። የሰላም ልኡካኑ በኢትዮጵያ በቆዩባቸው ዕለታት በአ

አቶ አበበ ጋሻው በዛ የኮሚቴው አባል ፣ በየተራ አብዮታ ችን ያስገኘላቸውን እኩልነትና አንድነት ፣ ፍቅር በመ ግለጽ ተናግረዋል ። በአጸፋውም ጳጳስ ዶክተር ካሮሊ ቶትና ብፁዕ መትሮፖሊታን ፊላሬት በተደረገላቸው ግብዣ ምስጋና አቅርበው ፣ ሃይማኖታውያን በዚሁ ዓይ ነት የአንድነት ርምጃቸውን እንዲቀጥሉ ሕዝባቸውንና አብዮታዊውን መንግሥት ከልብ እየረዱ የአገራቸውን ሰላምና አንድነት እንዲያስጠብቁ አደራ ብለዋቸዋል ።

ኅዳር ፳፪ ቀን እሑድ ጧት እንግዶቹ በመንበረ ጸባ ኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተገኝተው አስቀድሰዋል ። ከካቴድራሉ ዓውደ ምሕረት ሲደርሱ ብፁዕ አቡነ መቃ




ርዮስ የጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፣ ብፁዕ አቡነ ጎር ጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ አቶ መርስኤ ሐዘን አበበ የቤተ ክህነት ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጅ ፣ አስተዳዳ ሪው ሊቀ ሥልጣናት ገብረ ማርያም ፈለቀ ፣ የሰበካ ጉባኤ ዓባሎችና በካቴድራሉ የማኅበረ ክርስቶስ ዓባላት የሰ ላም ምልክት የሆነውን ርጥብ ዘንባባ ይዘው በመዝሙርና በይባቤ ተቀብለዋቸዋል ።

ጸሎተ ቅዳሴው እንደተፈጸመ ሊቀ ሥልጣናት ገ/ማ ርያም ፈለቀ በአውደ ምህረቱ ንግግር አድርገዋል ፤ ከዚያም በሰበካ ጉባኤው የተዘጋጀውን ስጦታ አበርክተዋል በኢትዮ ጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዋና ጸሐፊም ንግግር አድር ገው የመጽሐፍ ቅዱስ ስጦታ አበርክተዋል ።

ዜጠኞች የቀረበላቸውን ጥያቄ በደስታና በአጥጋቢ ሁኔታ መልሰው ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ከየመን ጉብኝት ሲመለሱ የተደረገላቸውን የአቀባበል ሥነ ሥርዓት ተመልክተው በታላቅ ክብር ተሸኝተዋል ።

መ ደ ም ደ ሚ ያ

፩ኛ/ በኢትዮጵያ አብዮት ከመደሰታቸው የተነሣ በ፲፱ ፹፩ ዓ/ም (በ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በመስከረም ወር በኢትዮጵያ የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብ ሰባ እንዲደረግ ጠይቀዋል ፤ ይህም ጥያቄአቸው በመንግሥ ታችን ተፈቅዶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር ስቲያን ግብዣውን ብትልክ መልካም ውጤት ይኖረዋል ።



ብፁዕ ወቅዱስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ለዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልኡካን የራት ግብዣና ንግግር ባደረጉበት ወቅት

መዘምራን ያሬዳዊ ዜማ አሰምተዋል ፣ ጳጳስ ዶክተር ካሮሊ ቶትና መትሮፖሊታን ፊላሬት በጠቅላላው በኢትዮጵያ በቆዩበት ጊዜ በተደረገላቸው አቀባበል የተሰማቸው ደስታ ከፍ ያለ መሆኑን ገልጸው የካቴድራሉ መርሐ ግብር አብቅቷል ።

፲፯/ በዚሁ ዕለት በቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ከጋ

፪ኛ/ የሰላም ልዑካኑ ጉብኝት የሐሰት ዜና አሠራጭ ዎችን ቅስም ይሰብራል ፣ እነርሱም በየሄዱበት ለኢትዮ ጵያ ሐቀኛ አብዮት በበለጠ እንዲናገሩ በጉብኝቱ የዓይን ምስክርነት አግኝተዋል ።

፫ኛ/ ከዚህ እንደተመለሱ ኢትዮጵያን ሳንደይ በሚል መነሻ ከዓባላት አብያተ ክርስቲያን ርዳታ ሰብስበው በኢ



www.ethiopianorthodox.org

ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በኩል ርዳታ እንደሚልኩ ታል ገብተዋል ።

፬ኛ/ ከኢትዮጵያ በአጸፋው ል ካን የሶሻሊስት አገሮ ችንና አብያተ ክርስቲያንን እንዲጎበኙ መርሐ ግብር አዘ ጋጅተው እንደሚጋብዙ ተናግረዋል ።

## አ ስ ተ ያ የ ት

፩ኛ/ ሐቀኞቹ ሐገር ወዳዶችና የሃይማኖት ድርጅቶች አንድነታቸውን አጠንክረው ለሰፊው ሕዝብ እንዲሰለፉ እንዲደረግ ፤

፪ኛ/ ትግል በእየቅጣጫው ነውና በመላው ዓለም በሚ ደረገው ግንኙነት ሁሉ ሐቀኞች የሃይማኖት ሰዎችም ስለአብዮታቸውና ስለሕልውናቸው ተረድተው እንዲያስ ረዱ ቢደረግ ጠቃሚ እንደሚሆን አይጠረጠርም ።

፫ኛ/ ብሔራዊ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች የሰላም ኮሚቴ እንዲቋቋም ቢፈቀድ ከትግል ከሰላምና ወዳጅነት ኮሚቴ ጋር በመተባበር ቢሠራ አብዮታውያንም በመካከሉ እየተ ገኙ የአመራር ሱታፌ ቢኖር በመላው ዓለም ካሉት ክርስ ቲያን ታጋዮች ጋር ግንባር በመፍጠር ብንሠራ ለአብዮታ ችንና ለሰፊው ሕዝባችን መልካም የሰላምና የብልጽግና ፍሬ እንደምናፈራ እናምናለን ።



# የ አ ቶ መ ር ስ ዔ ን ግ ግ ር

ክቡራን እንግዶቻችን ፤


ጳጳስ ዶክተር ካሮሊቶት ብፁዕ ሜትሮፖሊታን ፍላሬት የ1600 ዓመት እንጋፋ የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት መፈክሩ «ሰላም በምድር» ለሚለው ለጌታ ኢየሱስ ክር ስቶስ ምስጋና አቀርባለሁ ።

ለዓለም ክርስቲያን የሰላም ኮሚቴ ዓባሎችና ለሌ ሎች ጓዶች በዚህች ቦታ ላይ ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅድመ አብዮትና የአሁን ሁኔታ ባጭሩ ለመጥቀስ እወዳለሁ ።

እንደሌላው ሰፊ ሕዝብ ሲበዘበዙ የኖሩባት ቦታ ነች ፡፡

ንጉሡ ፤ መሳፍንቱና ለግል ጥቅማቸው የቆሙ የቤተ ክህ ነት ባለሥልጣኖች የሰፊውን ሕዝብ ንብረት በመበዝበዝ ሲንደላቀቁ ከግማሽ ሚሊዮን ያላነሱ ካህናት ግን በጢሰ ኛነትና በገባርነት ቀን እያረሱ ቤተክርስቲያንን የሚያገ ለግሉ ድርብ ጭቆና የነበረባቸው ወገኖች በቂ መጠለያ ልብስና ምግብ በማጣት በከፍተኛ ስቃይ ላይ ይገኙ ነባር ታዲያ የሲሶው መንግሥት ጋጋታ የሥዩማን እግዚአብሔር ተረት ነው ።

በምሥራቅ አፍሪካ የራሷ ፊደልና ቋንቋ ባለቤት የሆነ ችው ኢትዮጵያ የዚህች ቤተ ክርስቲያን ባለውለታ ነች ።



አቶ መርስዔ ኃዘን አበበ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ተ/ዋና ሥራ አስኪያጅ ለዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልዑካን በብሔራዊ የትያትር አዳራሽ ንግግር ሲያደርጉ ።

ከወደቀው ዘውድ አጠገብ የነበሩ በጣት የሚቈጠሩ የቤተ ክርስቲያን ልዑላንና መሳፍንት በተንደላቀቁበት ወቅት «ሲሶ መንግሥት ነበራት» እየተባለች የምትገመ ተው ቤተ ክርስቲያናችን ሠርቶ አደር ካህናትና መነኮሳት በአለው የሥነ ጽሑፍት የሥነ ጥበብና ሌላም ኪነታዊ ይዘት ፤ በሌላም የቱሪስት ዓይን ማራኪ በሆኑ ሕንጻዎችና ሐውልቶች ቤተ ክርስቲያኒቱ ስትመሰገን በጎስቋላና በተ በላሸ ሕይወት የሚኖሩ ልጆቿ እስከ የካቲት ፷፮ ዓ/ም



www.ethiopianorthodox.org

ድረስ ከሌላው የተለዩ አልነበሩም ። ከሌላው ባለመለየታቸው ነው ለአብዮቱ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በገንዘባቸውና በደማቸው ሳይቀር የተሰለፉት ፣ ኢምፔሪያሊዝም በአድዋና በሌሎችም ቦታዎቻችን የወረራ ሙከራ ባደረገ ጊዜ በግልጽ የተሰለፈች ቤተ ክርስቲያናችን ከአብዮቱ ወዲህ በነበረብን የኢምፔሪያሊዝም ከበባ ወቅትም ተሠልፋ ድርሻዋን አበርክታለች ።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ለሀገራቸው የደሙትና የቆሰሉት ከአምስት ዓመት በፊት ይቀጠቅጣቸውና ያስገብራቸው የነበረው ያ ጨቋኝ አገዛዝ እንዳይመጣባቸው ነው ። አሁንም ለወደፊቱም ከአብዮቱ ጎን ይቆማሉ ።

ቤተ ክርስቲያናችን ከአብዮቱ ወዲህ ፍጹም የሆነ ነፃነት ተጎናጽፋለች ። እንኳን ፓትርያርክና ጳጳሳት በዲሞክራሲ ለመምረጥ ቀርቶ የደብር አለቃ በጽሕፈት ሚኒስቴር ማዘዣ ይሾም የነበረበት ጊዜ ሩቅ አልነበረም ። አምስት ዓመት ነው ። ባሁኑ ሰዓት ቤተ ክርስቲያናችን ከአብዮት ወዲህ ማለት ነው ያለ አንዳች ተጽዕኖ አንድ ፓትርያርክና ፲፫ ጳጳሳት መርጣ ሾማለች ። በቅርቡ ሌሎችም ትመርጣለች ።

በአብዛኛው ክፍላተ ሀገር በቀበሌና የገበሬ ማኅበራት ሊቃነ መናብርት ቄሶችና ዲያቆናት ናቸው ። የቤተ ክርስቲያናችን ተከታዮች ያለ አንዳች ተጽዕኖ ለፈጣሪያቸውና ለአብዮቱ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ። ባንዳንድ ቦታ ጥቃቅን አለመግባባት ቢፈጠር እንኳ በውይይት እንፈታዋለን ። አብዮታዊውን መንግሥት በአግባቡ ጠይቀን ያጣነው ነገር የለም ። ወደፊትም ባግባቡ እንጠይቃለን ። ባግባቡ መልስ ይሰጠናል ።

ሰላም ፣ እኩልነትና ነፃነት እንዲኖር ቀድሞ የተሰበከ በቤተ ክርስቲያን ነበር ። «ፍትሕ ኀደለ ደሃ ተበደለ» እያሉ ነገሥታቱንና መኳንንቱን ይወቅሱ የነበሩ ሐቀኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ተገርፈዋል ፣ ታስረዋል ፣ ተሰደዋል ። ሰው በሰው መበዝበዝን ቤተ ክርስቲያናችን አጥብቃ ትቃወማለች ። እንግዲህ በሀገራችን በመካሄድ ላይ ያለው አብዮት ሰላምን ፣ እኩልነትን ፣ ፍትሕንና ዲሞክራሲን ሲያጠናክር ቤተ ክርስቲያኒቱ ትደሰታለች ።

ስለዚህ በሃይማኖት ስም የሀገርና የአብዮት ጠላቶች የሚያስወሩትን በየጊዜው ታወግዛለች እናንተም የሰላም ልኡካን ዋናው ዓላማችሁ ለዓለም ሰላምና ለሕዝቦች ዕኩልነት ስለሆነ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጎን ተሰልፋችሁ ለአብዮታችንና ለአገራችን አንድነት የሰጣችሁት ድጋፍ እንደማይለየን እናምናለን ። ኢትዮጵያን ምድራዊት ሲኦል እያስመሰሉ የሚያስወሩ ጠላቶቻችንን እንድትታዘቧቸው አጋጣሚ ጊዜ አግኝታችኋል ። በዓለም የሚደረገው የእኩልነትና የነጻነት ንቅናቄ በቅርጽና በሂደት ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መሆኑን የማየት እድል አግኝታችኋል ። በሀገራችን ቤተ ክርስቲያን ተዘግቷል እያሉ ጠላቶቻችን የሚያስወሩትን ሐሰተኞች በገሃድ ልትመለከቱት ችላችኋል ።

ቤተ ክርስቲያኒቱ የሰፊውን ሕዝብ ልጆች በማሳደግ የሙት ልጆችን በመንከባከብ በየቦታው የምታሳየው የልማት አስተዋፅኦ ለምሳሌ በመሠረተ ትምህርትና በመልሶ ማቋቋም ተግባር መሰለፏ ተግባሯን ለመወጣት ሞክራለች ትሩፋት እንደሠራች አትቈጠርም ። ወደፊትም ዓላማዋ ይህ ነው ። ታዲያ እናንተን ለመሳሰሉ ለሰው ልጆች እኩልነትና ሰላም ለሚደክሙ ሁሉ ምስጋና ታቀርባለች ባላችሁ አቋም የቤተ ክርስቲያናችንን ሁኔታ ለዓለም ገልጣችሁ ታሳያላችሁ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

አመሰግናለሁ ።

## የ ሊ ቀ ካ ህ ና ት ሰ ሎ ሞ ን ን ግ ግ ር

ብፁዕ ፍላሬት የኪብና የመላዋ ዑክራይን መትሮፖሊታን ፣ የምዕራብ አውሮፓ የፓትርያርክ እንደራሴና የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ሥራን የመቀጠል ኮሚቴ ሊቀ መንበር ።

ጳጳስ ዶክተር ካሮሊ ቶትስ በሁንጋሪያ የቡዳፔስት ጳጳስና የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ ሌሎችም የሰላም ጉባኤ መልእክተኞች ወንድሞቻችን

ጓዶች የሕዝባውያን ድርጅቶች ተጠሪዎች የየአብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ፣ የሰበካ ጉባኤ ዓባላት ፣ የእስልምና እምነት ተከታዮች ወንድሞቻችን ፣ እንዲሁም ወጣቶች

በዚህ ብሔራዊ የባህል አዳራሽ የተሰበሰብንበትን ምክንያትና መርሐ ግብሩን እንድገልጽ ይፈቀድልኝ ።

ምክንያቱ ግልጽና እውቅ ነው ። የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልኡካንን ለመተዋወቅ ነው ። የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ከ፪ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ቀዝቃዛው የርስ በርስ ጦርነት ጨርሶ ሳያከትም ከዛሬ ፳፩ ዓመት በፊት አርቀው በሚያስተውሉ ለሰው ልጅ ደኅንነት ፣ ሰላም ፣ እኩልነትና ነፃነት ፣ ትክክለኛ ፍትሕ በሚታገሉ ዓለም አቀፍ አስተሳሰብ በአላቸው ሰዎች በቸኮዝሎባኪያ ርእሰ ከተማ ፕራግ የተቋቋመ ሲሆን ዋና ጽ/ቤቱ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዚያው ጸንቶ ይኖራል ። የሰላም ቈጠማንም ለዓለም ሕዝብ እያበረከተ ሥራውን ቀጥሏል ፤ በአሁኑ ጊዜ እ ጅ ግ በጣም ተስፋፍቶ በጠቅላላው የዓለም ክፍል ቅርንጫፍ ያለው ከመሆኑም በላይ በብዙ ሀገሮች ብሔራዊ ኮሚቴ እያቋቋመ የሰላምን አውታረ ፀሐይ የዘረጋ ታላቅ ድርጅት ነው ።

ዝርዝሩን ከክቡራን እንግዶቻችን የምንሰማው ስለሆነ ለነርሱ እተዋለሁ ። ወደ ውድ አገራችን ኢትዮጵያ ታሪክ መለስ በማለት ማስታወስ ይፈቀድልኝ ለብዙ ዘመናት በፊውዶ ቡርዣ እግር ብረት ታ ስ ሮ የገዛ ምድሩ ያፈራችውን ሀብት እንዳይበላ አፉ ተለጉሞ በበሽታና በድንቁርና ሲገረፍና ሲሰቃይ የኖረው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በ፲፱፻፷፮ (በ፲፱፻፸፬) ዓ/ም በግብት ከመቅጽበተ ዓይን በፈነዳው አብዮት አማካይነት እንደከለባት ሲቧጭቀው የኖረውን የሞናርኪ አገዛዝ ደምስሶ ወደሶሻሊዝም በሚያሸጋግር ዲሞክራሲያዊ አብዮታዊ መርሐ ግብር የሰላም ጉባኤ የኮንቲኒዩሽን ኮሚቴ ሊቀ መንበር ፣ ጳጳስ ዶክተር ካሮሊ ቶትስ የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ዋና ፕሬዚዳንት ፣ ሬቨረንድ ክሪሲቲ ሮዛ የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ም/ዋና ጸሓፊና የእስያ የሰላም ጉባኤ ዋና ፕሬዚዳንት ፣ ሬቨረንድ ስታን ፎርድ ሻውሪ የታንዛኒያ አብያተ ክርስቲያን ምክር ቤት ዋና ጸሓፊና የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ዋና ጸሓፊ ፣ ካህን ላዛሩስ የፈረንሳይ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ዓባል የእንግሊዝ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ዓባል ። የዚህ ድርጅት አንቀሳቃሽ ኃይላት ናቸው ። እኛ ኢትዮጵያውያን በእናት



ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኰሚሽን ዋና ጸሓፊ ለዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልኡካን በብሔራዊ ቲያትር አዳራሽ ንግግር ሲያደርጉ ።

መመራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከውስጥም ከውጭም ብዙ ጠላቶች ተነሥተውበታል ። የምዕራባውያን የኤምፔሪያሊስት የሐሰት ወሬ ነኾሮዎች የሰፊውን የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ አብዮት ለመቀልበስ ሲሯሯጡ የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ስብሰባ በአደረገበት ሥፍራ ሁሉ የኢትዮጵያን አብዮት እንደደገፈ የኤምፔሪያሊስት ኃይላትን እንዳወገዘ ነው ፤ ዛሬ በመካከላችን የሚገኙት ታላላ ቅ እንግዶች ብፁዕ ፍላሬት የዓለም ክርስቲያኖች አገራችን ኢትዮጵያ ጥያቄ በኩል ምንም አይነት ፈ ተ ና ቢመጣ በሃይማኖት፣በጎሳ፣በቋንቋየሚከፋፍለን ኃይል የለም የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ዓላማና ግብ ይህ መሆኑን ስለምናውቅ እነዚህን የሰላም ልኡካን ለሰውልጆችመብት ነጻነት፣ሰላምና ትክክለኛ ፍትሕ የሚታገሉ ወንድሞቻችንን ስንቀበል እጥፍ ድርብ ደስታ ይሰማናል ። የፊውዶ ቡርዣውን ተባይ የሞላበት ጨርቅ አውልቃና አቃጥላ በሃይማኖት ፣ በጾታ ፣ በጎሳ ፣ በቋንቋ መለያየትን አስወግዳ





www.ethiopianorthodox.org

የእኩልነትን ፣ የነጻነትን ፣ የትክክለኛ ፍትሕንና የሰላምን የደመቀ ልብስ ለብሳ እያግረባት የሰፊውን ሕዝቧን ሀል ውና ለማጠንከር እየታገለች የውስጥና የ ውጭ ጠላቶቿን ያሸነፈችውንና ወደፊትም የምታሸንፈውን ፣ የሕዝቧንና የዓለምን ጭቁኖች ሰላም መሠረት ለማጽናት ገና ከፍተኛ ትግል ለመታገል ቆርጣ የተነሣችውን አዲሲቱን ውብ እናት አገር ኢትዮጵያን ለመጎብኘት እንደናት የሰላም ታጋ ዮች እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት በአገር ጉዳይ ሃይ ማኖት አይለያየንም ኮሚቴ ስም ልባዊ ደስታዬንበ ታላቅ ትሕትና እገልጻለሁ ። ከዚህ ቀጥሎ መርሐ ግብሩን በቅ ደም ተከተል እገልጻለሁ ።

## ከዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ከፍተኛ ልኡካን የተሰጠ አስተያየት

በአቡነ ዶክተር ካሮሊቶስ የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ፕሬዚዳንት የሚመሩት ልኡካን በኅብ ረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ የሚያደርጉትን የ፳ ቀናት የሥራ ጉብኝት ፈጽመው የመልስ ጉዞአቸውን ከመጀ መራቸው በፊት ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ በሰጡት መግለጫ በኅብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ በቆ ዩበት ጊዜና በተዘዋወሩበት ሥፍራ ሁሉ የተደረገላቸው አቀባበልና መስተንግዶ ከልብ ያስደሰታቸው መሆኑን ሰላም ወዳድ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት አም ስት መራራ የትግል ዓመታት በውጭና በውስጥ የተነሡ በትን ወራሪዎችና ቀልባሽ ኃይሎች አንበርክኮ አሁን ካለበት አስተማማኝ ደረጃ ሊደርስ በመቻሉና እንዲ ሁም አዲስ ሕይወትና ተራማጅ ሥርዓት በመገንባት ላይ መሆኑን በቅርብ ለመረዳት በመቻላቸው ያደረ ባቸውን አድናቆት ገልጠዋል ።

ከዚህም ሌላ ክርስቲያኖችና የሌሎችም ሃይማኖት ተከታይ ተባብረውና ተስማምተው ለአንዲት እናት ሀገር በማንኛውም የሥራና የትግል መስክ ሲሳተፉ ማየት ኢትዮጵያን ከፍተኛ ግምትና ክብር እንደሚሰጣት ልኡ ካኑ አመልክተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከአብዮታዊው መንግሥት ጎን ተሰልፋ ከምታካሄደው የዕድገትና ልማት ሥራ ሌላ ከሌሎችም የሃይማኖት ክፍ ሎችና ድርጅቶች ጋር ያላት ትብብርና ፍቅር ለሕዝቦች ሰላም ዕድገትና ብልፅግና ያላትን ቀና አመለካከት ያረ ጋግጣል ብለዋል ።

ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የጊዜ ያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር የሚኒስት ሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የአብዮታዊው ጦር ጠቅላይ አዛዥ ልኡካኑን ተቀብለው በማነጋገራቸው እና በዚህም ወቅት በአደረጉዋቸው የሐሳብ ልውውጦች ከልብ የተደ ሰቱ መሆናቸውን አስረድተዋል ። በተጨማሪም ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያክና ከቅዱስ ሲኖዶስ ዓባሎች ጋር ከሦስት ጊዜ በላይ ተገናኝተው የዓለምን ሰላምና ክርስቲ ያኖችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ያደረጉዋቸው ውይይ ቶች ያስደሰቷቸው መሆኑን ገልጸዋል ።

በአዲስ አበባ በልዩ ልዩ ሥፍራዎች በዝዋይና በደ ብረ ዘይት ባደረጉዋቸው ጉብኝቶች የተመለከቷቸው ተግ ባራት ሁሉ በአብዮታዊና በሰላም መሠረት ላይ የተዋቀሩ ሥፍራዎች መሆናቸውን ለመረዳት መቻላቸውን በተጨ ማሪ አስታውቀዋል ።

በዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ፕሬዚዳንት የሚመሩት ልኡካን በዚሁ መግለጫቸው ደብረ ዘይት ከተማ በሚገኘው የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አምባ ያደረጉት ጉብኝት አብዮቱን ከቅልበሳ ለማዳንና ዳር ድን በሩን ለማስከበር በመዋደቅ ላይ የሚገኘው አብዮታዊ ሠራዊት በደሙና በአጥንቱ ለከፈለው መሥዋዕትነት የኢ ትዮጵያ ን ሕዝብ በአዲስ ሥርዓትና ታሪካዊ ጉዞ በመም ራት ላይ የሚገኘው አብዮታዊው መንግሥት ተገቢ ክብ ሩንና ሀልውናውን እንደጠበቀለት አጉልቶ ያሳያል በማ ለት አድናቆታቸውን ገልጸዋል ።

ከዚህም ሌላ የወደፊቷን ኅብረተ ሰብአዊት ኢትዮ ጵያ ገንቢ የሆኑትን ታዳጊ ሕፃናት ተንከባክቦ እና በትም ህርት ኮትኩቶ ለማሳደግ በዝዋይ አካባቢ በመሠራት ላይ የሚገኘው የሕጻናት አምባ ያስደሰታቸው መሆኑን ጠቁመው ይህም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅ ላላ ጉባኤ ፲፱፻፸፱ ዓ/ም የሕፃናት ዓመት ሆኖ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲከበር ያሳለፈው ውሳኔ በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብና በአብዮታዊው መንግሥት ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አግ ኝቶ በተግባር በመተርጐም ላይ ለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ መሆኑን አስረድተዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የዓለም ክር ስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ለሚያካሄደው ተግባር የበኩ ሉዋን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ መሆንዋንም ልኡካኑ ገልጸው ፣ በዚሁም አኳያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክር ስቲያን ከድርጅቱ ጋር ባላት የቆየ ግንኙነት የድርጅቱን መልካም ዓላማ በማራመድ ረገድ ያልተቆጠበ ጥረት እን ደምታደርግ የዓይን ምስክር ሊሆኑ መቻላቸውንተናግረዋል

እነዚሁም የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ከፍ ተኛ ልኡካን ምዕራባውያን የዜና ማሰራጫዎች የሚያና ፍሱት ፕሮፓጋንዳ ሐሰት መሆኑን በአሁኑ ጉብኝታቸው ወቅት ሊያረጋግጡ መቻላቸውን አስታውቀዋል ።

ከጉብኝታቸው የተረዱት ቢኖር በኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት እኩልነት በተግባር እየተገለጠ ከመሆኑም ሌላ በልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል ፍቅርና መተባበር መኖሩን እንደሆነ አመልክተው ሕዝቡ ሃይማ ኖት ሳይለያየው በአንድነት ለአንድ ዓላማ በመሰለፍ በአሁኑ ጊዜ ነጻና ጠንካራ ኤኮኖሚ ለመገንባት በመረባ ረብ ላይ እንደሚገኝ በገሀድ ለመገንዘብ መቻላቸውን አረ ጋግጠዋል ።

ይህም የሚመለከተው ኢትዮጵያ የመረጠችው የኅ ብረተሰብአዊነት መመሪያ በልዩ ልዩ ሃይማኖት ተከታዮ ችና በአጠቃላይም በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ምን ያህል ተቀ ባይነት እንዳገኘ መሆኑን ገልጠው በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የዓለም ኅብረተሰብ በአሁኑ ጊዜ ሊቀስመው የሚገባው ብዙ ተደናቂ ነገሮች እንዳሉ አስታውቀዋል ።

ይህም በመሆኑ በማንኛውም ሥፍራና ጊዜ ይህንኑ እውነተኛ ገጽታዋን እንደሚያስረዱና የዓለም ኅብረተሰብም ኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ በትክክልና በመልካም የኅ ብረተሰብ ገንቢነትዋ እንዲያውቃት የበኩላቸውን ጥረት ከማድረግ እንደማይቆጠቡ አስረድተዋል ።

ልኡካኑ በዚሁ መግለጫቸው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አብዮታዊና ቆራጥ አመራር የሚያካሄደው የዕድገትና የብልፅግና ጉዞ የተቃና ውጤት እንዲያስገኝለት እንዲሁም በእኩልነት ላይ የተመሠረተው የልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች ትብብርና አንድነት ይበልጥ እየተጠናከረ እንዲሔድ ያላ ቸውን መልካም ምኞት ገልጸዋል ።

የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ልኡካን በኅብ ረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ለጉብኝት በቆዩባቸው ቀናት በተ መለከቱት ሁሉ እንደተደሰቱ አስታውቀው የልዩ ልዩ እም ነት ተከታዮች በአገር ጉዳይ ሃይማኖት አይለየንም በማለት አንድነት ፈጥረው ሃይማኖት ለሕዝቡ ተግባራዊ አገልግሎት ልትሰጥ በምትችልበት መንገድ ራሳቸውን ማዘጋጀታቸው በጣም አርድርጎ እንዳረካቸው ተናግረዋል።

## ፓትርያርኩ ለልደት በዓል ያስተላለፉት ቃለ በረከት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የ፲፱፻፸፪ ዓመተ ምሕረት ን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት ምክንያት በማድረግ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ማታ ከምሽቱ በሁለት ሰዓት ላይ በሬዲዮና በቴሌቤ ዥን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ቃለ በረከት አስተላልፈዋል ።

ባስተላለፉትም ቃለ በረከት ስለጌታችን መድኃ ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ከገለጹ በኋላ ስለ መላው ዓለም ሰላምና በተለይም በሀገራችን በኢትዮጵያ ከለውጡ ወዲህ ስለሚደረገው የሕጻናት እንክብካቤ ማለትም በሕ ጻናት ዓመት ላይ የተላለፈው ን መልእክት ቤተ ክርስቲያን የምትደግፈው መሆኗን አስገንዝበዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ለልደት በዓል ያስተላለ ፉት ቃለ በረከት ሙሉ ቃል ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ነው ።

<u>በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤</u>

ምስጋና ለእግዚአብሔር በሰማይ ሰላምም በምድር ይሁን ፤

የመድኅን ክርስቶስን በዓለ ልደት ለማክበር የተዘ ጋጃችሁ ምእመናን ለዚህ ዕለትና ሰዓት እንኳን በደህና አደረሳችሁ ፤

የልደትን በዓል ምክንያት በማድረግ ይህን መንፈሳዊ መልእክት ሳስተላልፍ ከዚህ ዕለትና ሰዓት በደህና አድርሶ ይህን በዓለ ልደት ለማክበር ላበቃን የዓለማት ፈጣሪ እግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ የክርስቶስ ልደት በመላ የክርስትና ዓለም ላይ በየዓመቱ በታላቅ መንፈሳዊ ደስታ ውየሚከበር እንደመሆኑ መጠን የኢትዮጵያ ምእመናንም በነገው ዕለት የልደትን በዓል በከፍተኛ መንፈሳዊ ስሜ ትና ደስታ አክብረው ይውላሉ ።

የዓለም ምእመናን የክርስቶስን ልደት የሚያከ ብሩት ያለምክንያት አይደለም ዐመፅና ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ «አለቅነቱ በጫ ንቃው ላይ የሆነ ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ» ተብሎ የሚጠራ (ኢሳ ፱ ፮) መድኅን እንደሚወ ለድና የድኅነት ቀንም እንደሚመጣ በዚያም ዕለት በድ ቀተ ኃጢአት የተነሣውን የድኅነተ ሥጋና የድኅነተ ነፍስ ፀጋ እንደገና እንደሚያገኝ በእምነት ተስፋ ይጠባበቅ ነበር ፤ ያም ተስፋ በክርስቶስ ተፈጽሟል ።

ይህም በመሆኑ የዓለም ምእመናን ሁሉ የክርስቶስን ልደት በደስታ ያከብራሉ ፣ በዚህም በእርግጥ የክርስቶስ ልደ ት የአዲስ ሕይወትና የድኅነት ቀን መጀመሪያ መሆኑን ይመሰክራሉ ፤ ከጽንፍ ጽንፍ አንድ ዓይነት የደስታ መዝሙርና የምስጋና ቃል በማሰማትም የዚህ ሐዲስ ሕይወት ውጤት የሆነውን አንድነታቸውን በተግባር ይገልጻሉ ።

መድኅን ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ «ሰላም በምድር» የሚል የምሥራች ዜና በምድር ላይ መሰማቱ የሰላምን አስፈላጊነት በበለጠ አጉልቶታል ። ይልቁንም በአሁኑ ጊዜ የሰላም ምሥጢር ለዓለም ግልጽ እየሆነ በመሄዱ የተነሣ «ሰላም በምድር» የሚለውም ቃል በአሁኑ ጊዜ የበለጠ ተሰሚነትን እያገኘ በመሆኑ የሚያስደስት ነው ። ሆኖም የሰው ልጅ በዓለም ላይ በሰላም ለመኖር የሚች ለው ሰላም ሊፈጠር የሚችልበትን የፍትሕና ርትዕ ተግ ባር በመፈጸም እንጂ በኀልዮና በተምኔት ብቻ አይደለም ። በዚህ ዓለም ላይ ሌላውን እንደራስ ከማየትና አንድ ሰው በራሱ ላይ ሊደረግ የማይፈቅደውን ነገር በሌላው ላይ ለማድረግ ካለመፍቀድ የተሻለ የሰላም ጎዳናም አይኖርም ።

ስለዚህ ለሰላም ኑሮ መሠረት የሆነው ይህ ፍትሕና ርትዕ በዓለም ላይ ይሰፍን ዘንድ የቤተ ክርስቲያን የዘወ ትር ምኞትና ጸሎት ነው ።





www.ethiopianorthodox.org

በእግዚአብሔር ፊት ሁሉም እኩል እንደመሆኑ መጠን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከበረውን የሕጻናት ዓመትና ለሕጻናት አስተዳደግ ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ የተሰጠውን ምዕዳን ቤተ ክርስቲያን ከልብ ትደግፋለች ፤ ሕጻናትን አትከልክሏቸው ወደእኔ ይምጡ ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነሱ ላሉ ናትና (ማቴ ፲፱ ፲፬) ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው ሁሉ ሕጻናት በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደዱና የተከበሩ የኅብረተ ሰብእ ክፍሎች በመሆናቸው ሕጻናት በተሟላ ሕይወት እንዲያድጉ በሚደረገው ጥረት ትተባበራለች ።

እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ በዚህች ለምለም ምድር ላይ ያኖረው ያለ ረሀብና ያለ ችግር እንዲኖር ስለሆነ ረሀብንና በሽታን ድንቁርናን ለማጥፋት በመካሄድ ላይ ያለውን የትምህርትና የልማት ተልእኮ እግዚአብሔር ይባርክልን ዘንድ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ትጸልያለች ።

በዓለም ላይ ረሀብና ችግር ሊወገድ የሚችለው ሰላምና ፍትሕ ሲኖር ስለሆነ የሰላም አምላክ ለዓለም ሰላምንና ፍቅር አንድነትን ይስጥልን ።

በዓሉን የደስታ በዓል ያድርግልን ።
አገራችን ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ይባርክ

# የዓለም ሕፃናት አባት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕፃናት ከፍተኛ ትኩረት እንደ ሰጠና አያሌ ልጆችንም ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ለልዩ ልዩ አገልግሎት እንደጠራቸው ከብሉያትም ሆነ ከሐዲሳት ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ መጥቀስ ይቻላል ።

በተለይም ራሱ ለቅርብ ተከታዮቹ ለደቀመዛሙርቱ ሲያስተምር « - - - እጁን እንዲጭንባቸውና እንዲጸልይ ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ ። ደቀመዛሙርቱም ገሠጹአቸው ። ነገር ግን ኢየሱስ ሕፃናትን ተውአቸው ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና» በማለት ኅብረተሰቡን ሕፃናትን በሆነ ባልሆነው ምክንያት ከመገሠጽ ይልቅስ ለሕፃናት ከፍተኛ እንክብካቤ ማድረግ እንደሚገባቸው አስተማረ ይህ ለማንኛውም ኅብረተ ሰብ የተሰጠ መመሪያ ነው ። በዚህ ትእዛዝ መሠረት የዓለም ኅብረተሰብእች ባላቸው አቅም ልክ ለሕፃናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ና እንክብካቤ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ። አብዮታዊት ኢትዮጵያ በውስጥና በውጭ የለየላቸው ጠላቶቿ በከፈቱባት ጦርነት ከአሁኑ ይበልጥ ልጆችዋን ለመንከባከብ ባትችልም ለታዳጊ ልጆቿ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ብዙ ተጨባጭ እንክብካቤዎችን ለሕፃናት እያደረገች ነው ። በይበልጥም አብዮታዊ መሪያችን ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ስለ አብዮታዊት ኢትዮጵያ ታዳጊ ልጆች ባላቸው ከፍተኛ ትኩረትና በየጊዜው በሚሰጡት ብሩህ መመሪያ ለአብዮታዊት ኢትዮጵያ ታዳጊ ልጆች ብዙ የማይረሱ እንክብካቤዎች በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር እንዲደረግ አድርገዋል ።

በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ሕፃናትን በምግብ በልብስ በትምህርትና በጤና በመሳሰለው የሚደረገው እንክብካቤና በመካሄድም ላይ ያለው እንቅስቃሴ ለአዛውንቶች ምነው እንደገና ሕፃን በሆንኩ የሚያሰኝ እንክብካቤ የተገኘው በቆራጡ መሪያችን ታላቅ መሥዋእትነት ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ፡ክርስቲያንም አቅመ ደካሞችንና ትምህርት ለመማር የሚፈልጉትን የአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ የተዘጋጀ ምግብ በመስጠት እንክብካቤ አድርጋ በጊዜው ይሰጥ የነበረውን ጥበብ እስከፈለጉበት ደረጃ ጊዜ ድረስ እንዲማሩ ያደረገች ናት። በዚህም ዕድል አያሌ ልጆች ተምረውበታል ። አሁንም ቢሆን እንደበፊቱ ባይበዛም በመጠኑ በዚሁ ዓይነት ዕድል በመጠቀም ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ልጆች በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ይገኛሉ ።

ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ ድርጊት በተለይ በአሁኑ ጊዜ ትምህርትን ለመከታተል የማይመች ኑሮውና ስሙ እንደሚያመለክተው በቆሎ ተማሪነት ለመማር የማይቻል በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን «ጠቦቶቼን ጠብቅ» የተባለውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ የዛሬዎቹ ለጋ ሕፃናት የነገይቱ ኢትዮጵያ ገንቢ መሆናቸውን ስለምታውቅ በይበልጥም ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የተገኙት የጭቁን ልጆች በመልካም እንክብካቤና በትምህርት ተስለው ማደግ እንደሚገባቸው ስለ አመነችበት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤን አቋቋመች ።

ለሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ መቋቋም መንሥኤው በወሎና በትግራይ ክፍላተ ሀገር ደርሶ የነበረው የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት አያሌ ሕፃናት የበድን ጡት እየጠቡ ወደ ሞት ጉዳና በማምራት ላይ ስለነበሩ ሕይወታቸውን ከሞት ለማዳን ቢሆንም አሁን ድርጅቱ በ ፮ ክፍላተ ሀገር ተስፋፍቶ በድርቅ በጦርነትና በመሳሰለው ምክንያት ያለተንከባካቢ የቀሩትን እጓለማውታዎች በመሰብሰብ እየተንከባከበች ታሳድጋለች ። ውዲቱ አገራችን እንኳንስ ለልጆቿ ለሌላም ሊተርፍ የሚችል ሀብት በማሕፀኗ ያላት ቢሆንም በነበረው ሰንካላ አስተዳደር ምክንያት የበይ ተመልካች የነበሩት ልጆቿ አያሌ እንደ ነበሩ የምናስታውሰው ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሕፃናት ለመርዳት ብትሞክርም በገቢ ማነስ ምክንያት የሚያግዛት አስፈለጋት ። በዚህ መሠረት በአላት ዓለም አቀፋዊ ግንኙነትና ተስሚነት ኪንደርኖትሄልፍ ከተባለው ክርስቲያናዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ጋር በመስማማት በድርቅ ፣ በጕርፍና በጦርነት ፣ በመሳሰለው ምክንያት ያለአሳዳጊ የቀሩትን ሕፃናት ልጆች በቅድሚያ በመቀበልና እናት ወይም አባት ኑሮአቸው በወላጆቻቸው ገቢ ማነስ ፣ በጤናና በመሳሰለው ምክንያት በቂ እንክብካቤ የማያገኙትን ሕፃናት በሁለተኛ ደረጃ ከመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች በኃላፊነት ተቀብላ ልጆቹ ሙሉ እንክብካቤ ተደርጎላቸው በቀለም ትምህርትና ከዚያም በኋላ በልጆቹ ፍላጎት መሠረት በሙያ ትምህርት ሠልጥነው ራሳቸውን እንዲችሉ ትረዳለች ።

ልጅ በወር ብር ፵ ብር በአንድ ዓመት ፩፻፹ ሂሣብ ኪንደርኖትሂልፍ እየተባለ ከሚጠራው ምዕራብ ጀርመን ከሚያገኘው ክርስቲያናዊ በጎ አድራጎት ድርጅት በሚያገኘው ርዳታ ነው ።

ኪንደርኖትሄልፍ በልዩ ልዩ አህጉራት በድርቅ በጦርነትና በጎርፍ በበሽታ በመሳሰለው ምክንያት ያለተንከባካቢ የቀሩትን ልጆች በመርዳት የታወቀ ዓለም አቀፋዊ ክርስቲያናዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ነው ።

የዚህ ክርስቲያናዊ በጎ አድራጎት ድርጅትና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስ



በደሴ ከተማ በአቡነ ጴጥሮስ ት/ቤት የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ከሚረዳቸው ዕጓለማውታዎች በከፊል

በዚህ ዓይነት እስከአሁን በያንዳንዳቸው ከ ፩፻-፳፻፴ ልጆች የሚይዙ ፲፱ አዳሪ ቤቶችን አቋቁማ ከ ፱፻ ፹ በላይ ዕጓለማውታ ሕፃናት ትንከባከባለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ሕፃናትን እየተንከባከበ የሚያሳድግበትን አስፈላጊውን ዕርዳታ ይኸውም በአንድ ተዳደግ ጉባኤ መመሪያ በማቴ ምዕ ፣ ፳፭ ፣ ቍ፡፵ ላይ «እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞች ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለኔ አደረጋችሁ» በማለት የተጻፈው ነው ።

በዚህ መሠረት በ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በወሎና በትግራይ ክፍለ ሀገር በደረሰው እልቂት ምክንያት ዘላቂ እንክብ





www.ethiopianorthodox.org

ካቤ የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት በየመጠለያውና በየመንደሩ ነበሩ ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ችግሩ ያጠቃቸውን ልጆች በዓላት አቅም ለመርዳት ብትሞክርም ይህ ርዳታ ሰፋ በአለ ሁኔታ መቀጠል እንደ አለበት ስለ ተረዳች ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት አደረገች ። በተለይም ሕፃናትን በመርዳት ረዥም ዕድሜና ልምድ ካለው ኪንደርናትሄልፍ ከተባለው ጋር በዚሁ ድርጅት ዋና ጸሐፊ በሚስተር ሉደር ሎወርስ አማካይነት ስምምነት አደረገች ።

ሚስተር ሉደር ሎወርስ የኪንደርናትሄልፍ ዋና ጸሐፊ ዳት በማስተባበር እስከአሁን ድረስ በርሳቸው ዋና ጸሐፊነት በሚካሄደው በዚሁ በኬንደርኖት ሄልፍ ክርስቲያናዊ በጐ አድራጎት ድርጅት ስር ከ ፳ ሺህ በላይ ችግረኞች ሕፃናት እየተረዱ በቀለም ከአንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅና በሙያ ትምህርት በኩልም በልዩ ልዩ የሙያ ትምህርቶች የሚሠለጥኑ ልጆች አሉ ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ሚስተር ሉደር ሎወርስ በ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በወሎና በትግራይ የደረሰውን ጉዳት በጊዜው ከቦታው በመገኘት ሁኔታውን በመመልከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የወንጌላዊት ቤተ



የዓለም ሕፃናት አባት ሚስተር ሉደር ሎወርስ

በዓለም ውስጥ በድርቅ በጦርነት ፣ በጎርፍ በእሳት ቃጠሎ በመሳሰለው ምክንያት ችግር የደረሰባቸውን ሕፃናት በመርዳት በተለይም በሕንድ አገር ደርሶ በነበረው ችግር ያለተንከባካቢ የቀሩትን ፴ሺ ሕፃናት ሰብስበው በኃላፊነት ሥራውን እየመሩ እየተንከባከቡ በማሳደግ የታወቁና የተፈተኑ ሐቀኛ ክርስቲያን ናቸው ።

ሚስተር ሉደር ሎወርስ በሕንድ አገር ብቻ ሳይወሰኑ ችግሩ በአለበት ቦታ ሁሉ ፈጥነው ከቦታው በመድረስና የሕፃናትን ሁኔታ ለርዳታ ሰጪ ግለሰቦች በማስረ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ሕፃናት በአዳሪ ቤት ገብተው በቂ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ቢያደርጉ ድርጅታቸው አስፈላጊውን ርዳታ እንደሚሰጥ በማረጋገጥ በገቡት ቃል መሠረት በአሁኑ ሰዓት ብዙ ሕፃናት በዚሁ ዕድል እየተጠቀሙ ናቸው ።

ሚስተር ሉደር ሎወርስ ከአብራካቸው የወጡ ፪ ልጆች ያሉዋቸው ቢሆኑም በ፳፰ አዳሪ ፸፩ ቤቶች ያሉትን አያሌ ልጆች ልክ እንደራሳቸው አድርገው የሚ



ወዱና የእነዚህ ሁሉ ልጆች አባት በመሆናቸውም ደስ የሚላቸው ናቸው ።

ስለ ኢትዮጵያም ታላቅ ፍቅር ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ ችግሩ በአለበት ሁሉ አዳሪ ቤቶች ተከፍተው ራሳችንን በራሳችን ከምንረዳበትና ርዳታ ከማንሻበት ደረጃ እስክንደርስ ድረስ በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር ለመርዳት ሙሉ ፍላጎትና ፈቃደኛ የሆኑ ሐቀኛ ወዳጃችን ናቸው ።

ሚስተር ሉደር ሎወርስ ከጥር ፭ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ጥር ፳፭ ቀን ፸፱ ዓ/ም ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ እስከአሁን ያሉትን የሕፃናት ማሳደጊያ አዳሪ ቤቶች የሥራ ሁኔታ ለመመልከት በይበልጥ ተስፋፍተው ብዙ ልጆችን በመቀበል በቀለምም ሆነ በሙያ ትምህርት ይኸውም ኢትዮጵያ በምትፈልገው የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅጣጫ ሠልጥነው ውዲቱ አገራቸውን የሚያገለግሉበትን ለመቀየስና እስከአሁን ድረስ ለአዳሪ ቤት የሚሆን ቤት ከመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ባለማግኘት አዳሪ ቤት ባልተከፈተባቸው ቦታዎች የሚከፈትበትን መንገድ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፣ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና የየአዳሪው ቤት ሊቃነ መናብርት ከአቶ መርስዔ ኀዘን አበበ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ተ/ሥራ አስኪያጅና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ሊቀ መንበር ፣ ከጉባኤው ዓባላት ፣ ከአዳሪ ቤቱ ኮሚቴ ዓባላትና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሁሉ ጋር ለመወያየት በመካከላችን ይገኛሉ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደገለጽነው ።


ርዳታው አሁን በአሉት ብቻ ሳይወሰን ወደፊት በድርቅ በጦርነት በገቢ ማነስና በመሳሰለው ምክንያት በቂ እንክብካቤ ያላገኙትን ልጆች ከመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች በኃላፊነት እየተቀበልን ፣

፩ኛ/ ዕድሜያቸው ከ ፺—፲፩ ዓመት የሆኑትን ሴት ልጆች በአዳሪ ቤት ተቀብለን በየትኛውም ት/ቤት ገብተው በቀለምና በሙያ ትምህርት ሰልጥነው ራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ ለመርዳት ፣

፪ኛ/ ዕድሜያቸው ከ ፬—፺ ዓመት ያሉትን ልጆች በመዋዕለ ሕፃናት ተቀብለን ቀን ቀን በመዋዕለ ሕፃናት ምግብ ልብስ ትምህርትና የመሳሰለው እየተሰጣቸው ከዋሉ በኋላ ማታ ከቅርብ አሳዳጊዎቻቸው ዘንድ ሄደው እያደሩ እንዲረዱ ለማድረግ ፣

በ፩ኛ ተራ ቊጥርና በ፪ኛ ተራ ቊጥር ለተዘረዘረው ርዳታ አገልግሎት የሚውል ቤት ከመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ከተሰጠን በእኛ በኩል ዝግጁ ነን የርዳታ ሰጪ ድርጅቶችም ሁሉ በሙሉ ይተባበሩናል ።

በተለይም ኢትዮጵያን የሚወዱት ሚስተር ሉደር ሎወርስ ለዚህ ቆርጠው የተነሡ ናቸው ።



ሚስተር ሉደር ሎወርስ አዲስ አበባ ሲገቡ አቶ መርስዔ ኀዘን አበበ የቤተ ክህነት ተ/ ዋና ሥራ አስኪያጅና አቶ ፀጋዬ በርሄ የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ ተቀብለዋቸዋል ።




www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን ካህናትን ለማደራጀት ከፍተኛ ጥረት በማድ ረግ ላይ መሆኗን ፓትርያርኩ ገለጡ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ/ም ከቀኑ በ፲፩ ሰዓት ላይ በጸሎት ተከፍቷል ።

ይኸውም የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ የመክፈቻ ሥር ዓቱ ጸሎት የተከናወነው በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ



ቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባውን በማካሄድ ላይ እንዳለ

ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲሆን በሥርዓተ ጸሎቱ ላይ የቤተ ክህነት ሹማምንትና የመምሪያ ኃላፊዎች ፣ የአድባራት አስተዳዳሪዎችና የገዳም አበምኔቶች የሰ ፣ በካ ጉባኤ ሊቃነ ካህናትና ሊቃነ መናብርት እንዲሁም የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ተገኝተዋል ።

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ

ሲኖዶስ ጉባኤ ሊቀ መንበር መሪነት የመክፈቻው ሥር ዓተ ጸሎት ተከናውኖ እንዳበቃ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያ ርኩ የቅዱስ ሲኖዶስን ዓላማ በማስመልከት ቃለ በረከት አሰምተዋል ።

ቅዱስነታቸው ባሰሙትም ቃለ በረከት ጥንታዊቷና ታሪካዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የብ ዙኃን እናት መሆኗን ጠቅሰው ውለታዋን ለመመለስ መጣ ጣርና የሚፈለገውን አስተዋፅኦ ሁሉ ለማድረግ መሽቀዳ ደም የተከታዮቿ ሁሉ ድርሻ መሆኑን አስገንዝበዋል ።

ቅዱስነታቸው አያይዘው በሰጡት ቃለ በረከት ባለ ፈው ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን የነበረችበትን ሁኔታ አስ ታውሰው ቀድሞ የጥቂቶች የነበረችው ቤተ ክርስቲያን አሁን ግን በአዲሱ ሥርዓት የብዙኃን ቤተ ክርስቲያን ለመሆን መብቃቷን አስረድተዋል ።

ቅዱስነታቸው በሰጡት ተጨማሪ ቃለ በረከት የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከአሥራ ስም ንት ሚሊዮን በላይ ተከታይ ፣ ከአሥራ ስምንት ሺህ በላይ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንና ከሁለት መቶ ሺህ በላይ አገልጋ ዮች ካህናት ያሏት ዝነኛና ገናና ቤተ ክርስቲያን መሆኗን አውስተው በአሁኑ ሰዓት በኅብረተሰብአዊነት ያመራር ፍልስፍና መሠረት በነጻነት መድረክ ላይ ቁማ ስለ ምት ገኝ በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ አማካይነት እራሷን በራሷ ለማስተዳደርና አገልጋዮቿ ካህናትን ለማደራጀት በየ አቅጣጫው የምታሳየው የሥራ እንቅስቃሴ ሁሉ በቀላሉ የማይገመት መሆኑን ገልጸዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ባሰሙት የማጠቃለያ ቃለ በረከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር ስቲያን ተከታዮች የሆኑ ምእመናን ሁሉ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን እንዲሁም ገንዘባቸውን በማስተባበር የተ ቀደሰ ድጋፋቸውን እንዲያደርጉላትና ሌሎች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ከደረሱበት ደረጃ ላይ እንዲያደር ሷት አባታዊ ምክራቸውን ለግሠዋል ።

በአለፈው ጥቅምት ወር መጀመሪያ ይደረግ የነበረው ይኸው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በአንዳንድ ችግሮች ምክ ንያት በአሁኑ ወቅት እንዲደረግ የተዛወረ መሆኑንና በዚሁ ጉባኤ በልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይ ይት ተደርጎ ውሣኔ እንደሚተላለፍ ለመረዳት ተችሏል።

## ቅዱስነታቸው የሰጡት ቃለ በረከት ሙሉ ቃል

ይህች ጥንታዊትና ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያናችን ያላሳደገችውና ያላቀፈችው ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ባለ መኖሩ በእኩልነት የሁሉ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን እና የብዙዎች እናት እንደ መሆኗ መጠን ቀሳውስትና ዲያቆናት በማጥመቅና በማቁረብ መዘምራን በማኅሌት ምእመናን በአሥራቱና በሙዳየ ምጽዋቱ እኩል ያገለግ ሏታል ።

ቤተ ክርስቲያን የሁላችንም ከሆነች በየአቅማችን ማገልገል አለብን በውስጧ አድገ እንደችሎታው የአገል ግሎት አስተዋፅኦ የማያደርግ ምእመን ካለም ከፍተኛ ዕዳ አለበት ።

ባለፈው ሥርዓት ቤተ ክርስቲያናችን የነበረችበትን ሁኔታ መለስ ብለን ስንመለከተው በጥቂት ሰዎች እጅ ብቻ ነበረች አሁን ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉም ባንድነት ተባብሮ እንዲአነሣት ዕድል ስለገጠማት ጥሪ ዋን ታሰማለች ።

ቤተ ክርስቲያናችን በሀገር ውስጥ ከ፲፰ ሚሊዮን በላይ የሆኑ ተከታይ ከ፲፰ ሺህ በላይ ሕንፃ ቤተ ክርስቲ ያንና ከ፪፻ሺህ በላይ ካህናት ያላት ሰፊና ገናና ናት ።

ይህን ያህል ስፋትና ድምቀት ያላት ስትሆን በው ስጧ ያሉትን ካህናትንና ምእመናንን የሚያቀራርብና አንድ የሚአደርግ ሥርዓት ባለመኖሩ መቀራረባቸው በመጠኑ በመሆኑና ያላት ሀብትም በጥቂት ሰዎች ሆኖ ዘመኑ በሚ ጠይቀው መሠረት መንፈሳዊ ት/ቤቶች ተደራጅተው ካህናትን በጥራት ለማዘጋጀት ባይቻልም ሕዝቡ ባለው መንፈሳዊ ፍላጎት ብቻ ከየቤተ ክርስቲያኑ ካሉት ሊቃ ውንቶች እየተዘዋወሩ ተምረው በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ያለው ገቢ በትክክል በእጁ ስለማይገባ በስሟ የተማረ ሁሉ በተለያየ የሥራ መስክ ተሠማርቶ ሀገሩን ሲረዳ በውስጡ ያለው መንፈሳዊ ናፍቆት እያስገደደው አቅሙ በሚፈቅደው መሠረት ርዳታ ከማድረግና ከማገልገል እጁን አላጠፈም ።

እነሆ ዛሬ ነፃ ቤተ ክርስቲያን ሆና የራሷን አመራርና አስተዳደር በራሷ እንድትወጣ ዕድል ስለገጠማት ካህኑን መዘምሩንና ምእመናኑን አስተባብሮ አንድ የሚአደርግ መመሪያ አውጥታ የራሷን አስተዳደር በመምራቷ የሚታ የው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ቀላል አይደለም ።

ይህ ሁኔታ በዚሁ ቀጥሎ ሁላችንም አንድነታችንን አጥብቀን መንፈሳዊ ጉዞአችንን በዚሁ ከቀጠልን በቅ ርብ ጊዜ ውስጥ መንፈሳዊ ኮሌጆችንና ሌሎችንም መደ ረግና መዘጋጀት የሚገባቸውን ሁሉ እንደ ምናደርግ እና ምናለን ።

እጉ ዘይትራዳዕ ምስለ እጉ ይመስል ከመ ሀገር እንተባ ጥቅም እንደተባለው እውቀቱንና ጉልበቱን አንድ ያደገረ ወገን ሁሉ ከባዱን ነገር ሁሉ ይወጣል ። ይህም ከሆነና ከተረዳን ሁላችንም እንደየአቅማችን እንደችሎታችን በገንዘብ በሐሳብ በምክርና በጸሎት ከተረዳዳን ቤተ ክርስ ቲያናችንን ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ከሚጠብቁብን በላይ በቀላሉ ልናደርሳት እንችላለን ።

ከሁሉ በፊት ግን ለቤተ ክርስቲያናችን አንድነት መጠናከርና መስፋፋት ለመንፈሳውያን ወጣቶች ልንታገል የምንችለው ከእያንዳንዳችን ሕሊና ግላዊ ነትንና ጠባብነትን ስናስወግድ ነው ።

ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ወንድ ሴት ሕፃን ሽማግሌ ክር ስቲያኖች ሁሉ እንድንተባበር ቤተ ክርስቲያናችን ድም ፅዋን ታሰማለች ይልቁንም በኃላፊነት ላይ ያለን ካህናት ይህንን ተግባር ፈጽመን ለማስፈጸም ከፍተኛ ጥረት ይጠበቅብናል ሲሉ ቅድስና የተመላውና በረከታዊ የሆነ ምክራቸውን ለመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ምእ መናን አስተላልፈዋል ።





www.ethiopianorthodox.org


# ስለመንፈሳዊ ኮሌጅ ተቋም መሻሻል ፓትርያርኩ በተገኙበት ውይይት ተደረገ

እያሌ ምሁራንን በማፍራት ለረጅም ዘመናት ሰፊ አገልግሎት ስለአበረከተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኮሌጅ ተቋም መሻሻልና በዘመናዊ አቅድ መደራጀት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በተገኙበት ታኅሣሥ ፳ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም እሁድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ከፍተኛ ውይይት ተደርጓል ።

በውይይቱም ላይ የቅዱስ ሲኖዶስ ዓባላት ፣ የቤተ ክህነት ፣ የልማት ኮሚሽን ፣ የሃይማኖተ አበውና የሐዋርያዊ ድርጅት ሹማምንት እንዲሁም የኮሌጁ ድኅረ ምሩቃንና ከልዩ ልዩ ድርጅት ጥሪ የተደረገላቸው ከፍተኛ ምሁራን ተሳትፈዋል ።

ስለ ውይይቱ በወጣው መርሐ ግብር መሠረት በተጠቀሰው ዕለት ከጧቱ በ፬ ሰዓት ላይ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጸሎተ ቡራኬ ጉባኤው ተከፍቶ በመጀመሪያ ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ዋና ጸሓፊ የጉባኤውን ዓላማ ከገለፁ በኋላ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት ጳጳስ ቅዱስ ሲኖዶስን በመወከል ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ ዓላማና ተግባር እንዲሁም በመንፈሳዊ ኮሌጅ ተቋም ላይ ስለሚኖረው ኃላፊነትና ሚና በዝርዝር አስረድተዋል ።

ቀጥሎም ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ዋና ጸሓፊና አቶ ሐዲስ ተረፈ የካህናት ማሠልጠኛ ኃላፊ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ በጠቅላላ ለሀገሪቱ ስለአበረከተው ሰፊ አገልግሎት በመጥቀስ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ አማካይነት ወደፊት የዚሁ ኮሌጅ ተቋም ለማሻሻልና ባዲስ መልክ ለመመሥረት የተደረገውን ጥናትና እቅድ በመተንተን አስረዱ ፣ ከዚያም ጉባኤው ውይይቱን ቀጥሎ በቀረበው ጥናትና እቅድ ላይ አንዳንድ ሐሳቦችን ጨምሮ በማጽደቅ ውይይቱን አብቅቷል ።



ስለመንፈሳዊ ኮሌጅ ተቋም መሻሻል ውይይት በተካሄደበት ወቅት

በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ የምሁራን ግንኙነትና ውይይት ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለሀገር የሚበጅ መሆኑን ጠቅሰው ጸሎተ ቡራኬ ካደረጉ በኋላ ጠቅላላ የጉባኤው ፍጻሜ ሆኗል ።

# የጎንደርን ካህናት ከርእዮተ ዓለም ጋር ለማገናዘብ ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን ጓድ ሻለቃ መልአኩ ተፈራ አስገነዘቡ

ኅብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ በሣይንሣዊ ሶሻሊዝም መርሖ እንድትመራ ሲታወጅ ማንኛቸውም ሃይማኖቶች በብሔራዊ ደረጃ በእኩልነት እንዲከበሩ ተደርጓል ፤ በተለይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ሲወጣ የሃይማኖቶችን እኩልነት አብዮታዊው መንግሥት አውጆአል ።

በዚሁ መሠረት በጎንደር ክፍለ ሀገር የሚገኙትን ካህናት ከርእዮተ ዓለም ጋር ለማገናዘብ ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑንና በማንኛቸውም ታዋቂ ሃይማኖቶች ላይ የፖለቲካ ተጽዕኖ እንደማይደረግ ጓድ ሻለቃ መልአኩ ተፈራ የጎንደር ክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳሪ አስገነዘቡ ።

ጓድ ሻለቃ መልአኩ ተፈራ ፣ ይህን ማስገንዘቢያ የሰጡት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየሳምንቱ እሑድ እየታተመ የሚወጣው የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ አዘጋጅ ቡድን ለሦስት ወራት ያህል የመንፈሳዊና የርእዮተ ዓለም ኮርስ በተከታተሉ የጎንደር ርእሰ ከተማና የአውራጃዎቹ ሊቃነ ካህናት የምረቃ በዓል ላይ ከተገኘ በኋላ በአጋጣሚ ከጽ/ቤታቸው ተገኝቶ በጎንደር ክፍለ ሀገር በሚገኙት ካህናት ወይም የሃይማኖት ሰዎች ላይ ስለአለው የርእዮተ ዓለም አመለካከትና ጠቅላላ ህልውና ላቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ነው ።

ጓድ ሻለቃ መልአኩ ተፈራ በዚሁ ጋዜጣዊ መግለጫቸው ላይ በጭቁኑና በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከንድ ተመትቶ የወደቀው የቀድሞው አድኃሪ ና በዝባዥ መንግሥት ለይስሙላ «ሀገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው» የሚለውን ተግባር አልባ መፈክር በአንድ በኩል እያሰማ በሌላ በኩል ደግሞ በየገዳማቱና በየደብሩ በጠቅላላው በመንፈሳውያን ቦታዎች በአምባገነንነት እጁን እየሰደደ ፣ የመንፈሳውያን ኅብረተ ሰቦችን ድርሻ ይበዘብዝ ስለነበረ ጭቁን ካህናት የሙያቸውንና የአገልግሎታቸውን ዋጋ ተነፍገው የበይ ተመልካች ሆነው መኖራቸውን ጠቅሰው በአሁኑ ወቅት ግን አብዮቱ የመጣው ለሌላው ጭቁን ኅብረተሰብእ ብቻ ሳይሆን በየደጀሰላሙና በየመቃብር ቤቱ በአስከፊ ሁኔታ ወድቆ ለሚገኘው ወገን ሁሉ ስለሆነ በአብዮታዊው መንግሥት አዋጅ መሠረት በጎንደር ክፍለ ሀገር የሚገኙት ገዳማትና አድባራት በአጠቃላይ የሃይማኖት ሥፍራዎች ይዞታ በራሳቸው ኃላፊነት ፣ የተከበረ ፣ መሆኑን ገልጸዋል ፤ እንዲሁም በእርጅና ምክንያት ደጋፊ በማጣት ለወደቁት አባቶችና ለተቸገሩ ገዳማት የክፍለ ሀገሩ አስተዳደር የተቻለውን ርዳታ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ አስረድተዋል ።

ጓድ ሻለቃ መልአኩ ተፈራ በሰጡት ተጨማሪ መግለጫ የጎንደር ክፍለ ሀገር የመንፈሳዊው ትምህርት ማስመስከሪያዎች የሚገኙበት ፣ እንደመሆኑ መጠን እያሌ መንፈሳውያን ምሁራንን ያቀፈና በርከት ያሉ ገዳማትንና አድባራትን የያዘ በመሆኑ ራሳቸው አረጋውያን ሊቃውንቱም ቢሆን እንደታሪክ ቅርስ የሚቈጠሩ በመሆናቸው በመንፈሳዊው አቋም አንጻር የጎንደር ክፍለ ሀገር አስተዳደር ከፍተኛ እንክብካቤ ያደረገላቸውና በማድረግ ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቁመው አብዮቱ ከመጣባቸው ከአንድ አንድ የቀድሞ መኳንንትና መሳፍንት ማዕድ ባራኪዎች ከሆኑ መሳይ መንፈሳውያን የለውጥ እንክርዳዶች በስተቀር የመንፈሳዊው ን አርበኛ የአቡነ ጴጥሮስን አርአያ የተከተሉ እያሌ የቤተ ክህነት ሰዎችና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ከታጋይ አብዮታውያን ጓዶች ጎን በመሰለፍ ለአብዮት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያበረከቱና መሥዋዕትነትን የከፈሉ መሆናቸውን ካስገነዘቡ በኋላ በአንጻሩ ደግሞ እንደ ጳንጠቆስጤና እንደ ጂሆባ የመሳሰሉት የምዕራባውያን ደቀ መዛሙርት ከየፀረ አብዮቱ ካምፕ በመሰደድ በሃይማኖት ስም ቤተ ክርስቲያንን ተጠግተው ፀረ አብዮት ሴራ በማካሄድና ያልሆነ ውዥንብር በመንዛት ላይ ስለሚገኙ እንደእነዚሀ ባሉት ፀረ ሕዝቦች ላይ ከአብዮታዊው መንግሥት አስቀድሞ ኃላፊነት የተጣለበት ቤተ ክህነት አስቸኳይ ርምጃ መውሰድ እንዳለበት አሳስበዋል ።

ጓድ ሻለቃ መልአኩ ተፈራ ማስገንዘቢያቸውን በመቀጠል በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችም በኩል በቀድሞው ጨቋኝ ሥርዓተ ማኅበር ጊዜ «የእስላም አገሩ መካ የወፍ አገሩ ወርካ «እየተባለ ይጠቀስ የነበረው አነጋገር እንደሚያስረዳው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በሆኑት ኢትዮጵያ ውያን ወገኖቻችን ላይ የቱን ያህል ጭቆና እንደነበረ አውስተው በዚህም አንጻር በጎንደር ክፍለ ሀገር በሚገኙ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችና በመሳሰሉትም የታወቁ ሃይማኖቶች ላይ የፖለቲካ ተጽዕኖ እንደሌለ አስረድተዋል ።

ስለዚሁ ስለመንፈሳዊው አቋም ና ስለ ሃይማኖት ሰዎች ከኅብረተሰብአዊ ህልውና ጓድነታቸው በሰጡት አጠቃላይ መግለጫ የአብዮታችን ግቡን መምታት ተስፋ ያስቆረጣቸው ጠላቶቻችን እንደሚነዙብን ውዥምብር ሳይሆን በአሁኑ ወቅት በጎንደር ክፍለ ሀገር ባለው የፖለቲካ ይዘት ፳፩ በመቶ የእረንጓዴው ትርኢት ፕሮግራም ማለት የልማቱ ሥራ በተፋጠነ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ስለሆነ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር በወንድማማችነትና በእኩልነት ተሳስሮ እንዲኖርና እንዲሁም ጥሮ ግሮ የላቡን ወዝ እንዲ





www.ethiopianorthodox.org

በላ የተደነገገው በኅብረተሰብአዊ ነት አመራር ፍልስፍና ብቻ ሳይሆን ይህ ዓይነቱ ቀና አስተሳሰብ በሃይማኖትም ፍልስፍና ሥፍራ የተሰጠው ስለሆነ ቀዳሽና አምራች የሆ

ተከክለ ይሁን» በማለት ለሌላው የሚናገሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ተግባራዊ ሆኖላቸው እነሱም እንደሰፊው የኢትዮጵያ ፣ ሕዝብ የነፃነት አየር እንዲተነፍሱና በማን



ጓድ ሻለቃ መልአኩ ተፈራ የጎንደር ክፍለ ሀገር ዋና አስተዳዳሪ ለዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጠኞች ቡድን መግለጫ በሰጡበት ወቅት ።

ኑትን ካህናት በልማቱ ተግባር ይበልጥ ለማሳተፍና የርእዮተ ዓለም አመለካከት እንዲኖራቸው ለማድረግ ፤ ብሎም «ተራራው ዝቅ ይበል ፣ ጎድጓዳው ይሙላ ሁሉም የተስ

ኛውም አቅጣጫ የእኩልነት ኑሮ እንዲኖሩ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን አስገንዝበዋል ።

# የመ ጀመሪያው ዙር የአፍሪካ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ

የመጀመሪያው ዙር የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ስብሰባ ከታኅሣሥ ፲፩ እስከ ታኅሣሥ ፲፯/፲፱፻፸፱ ዓ/ም ድረስ በማዳጋስካር ዋና ከተማ ታናናሪብ ሲካሄድ ሰንብቷል ። የጉባኤው ተሳታፊዎች ከመላው አፍሪቃ ፣ ከእስያና ከአውሮፓ የመጡ ነበሩ ።

ከዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ መሪዎች መካከል ዶክተር ካሮሊ ቶት የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ፕሬዚዳንት ፤ ዶክተር ሚርየብስኪ የዓለም ክርስቲኖች የሰላም ጉባኤ ዋና ጸሐፊ እንዲሁም ከደቡብ አፍሪቃ ፣ ከናሚቢያ ዚምባብዌ የነፃነት ትግል ዓባሎች ከመገኘታቸውም በላይ የሞሪየሽና የሪዩኒየን ደሴቶች ተወካዮች በእንግድነት ጉባኤውን ከተሳተፉ በኋላ ሙሉ ዓባላት እንዲሆኑ ተፈቅዶላቸዋል ።

ጉባኤው የተመራው በዶክተር ሪቻርድ አንድሪማንጃቶ የማዳጋስካር ሬቡሌሽን (አብዮት) የበላይ ምክር ቤት ዋና ዓባል ሊቀ መንበርነት ነበር ። በጉባኤው መከፈቻ ወቅት የማዳጋስካር መንግሥት የሱፐርም (የበላይ) ምክር ቤት ዋና ዓባል የሆኑ በማዳጋስካር መንግሥትና በፕሬዚዳንቱ ስም ንግግር አድርገው ጉባኤውን ከፍተዋል።

ጉባኤው በአራት ዕለታት ስብሰባው ሰላምን ስላናጉና ስለሚያናጉ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች በተለይም ስለ አፍሪቃ ችግር ከልዩ ልዩ ተናጋሪዎች ሪፖርር አዳምጧል ። በፍጻሜውም ቀጥሎ በተመለከቱት ዐበይት ነጥቦች ተስማምቶ መግለጫ አውጥቷል ።

በነፃነት ጥያቄ ፣

፩/ የዜምባብዌን ሰላማዊ ህልውና በሚመለከት ጉዳይ ላይ በለንደን ውይይት እየተደረገ መሆኑ ግልጽ ነው ። የናሚቢያንም እድገትና የፍጹም ነፃነት ርምጃ የሚመለከትም ጉዳይ በተስፋ ይጠበቃል ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ውሳኔ እንዲሆንም ያሻል ፣ የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ የዜምባብዌን ነፃ አውጭ አርበኞች ግንባር የሚያደርገውን የነፃነት ትግል በሙሉ ልብ ይደግፋል ፣ ከመላው ታጋይ የዜምባብዌ ሕዝብ ጋር አብሮ ያለ መሆኑንም አብሥሯል ።

በናሚቢያ ስለአለው ይዞት በዓለም መንግሥታት ማኅበር በጸጥታ ጥበቃ በኩል በ፬፻፴፭ኛው ውሳኔ የተላለፈውን በሁሉም በኩል ተቀባይነት በማግኘቱ የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤም የተቀበለውና የሚደግፈው መሆኑን አስታውቋል ።

ጉባኤው የዜምባብዌን ድንበር ጥሰው በመግባት የደቡብ አፍሪቃ ምንደኞች የቦምብ ናዳ እያወረዱ የሚያደርጉትን ጥፋት አውግዟል ።

የደቡብ አፍሪቃ ዘረኛና ቀለመኛ መንግሥት የተያያዘውን ሕገ ወጥ የአፓርታይድ ድርጊቱን እንዲያቆም (እንዲያከትም) ጉባኤው ጠይቋል ።

የደቡብ አፍሪቃ ጥቂቶቹ ባለሥልጣኖች ሥራዬ ብለው የያዙት የአፓርታይድ ይዞታቸው ለዓለም ሰላም ጠንቅ መሆኑን ጉባኤው አስገንዝቧል ። የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ የምዕራብ መንግሥት ሕዝባውያን ድርጊቶች ባንኮች ለደቡብ አፍሪቃ (ዘረኛ መንግሥት የሚያደርጉትን ርዳታና ማንኛውንም ግንኙነታቸውን እንዲያቆሙና ዘረኛው የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት የአፓርታይድ ፖሊሲውን እንዲያቆም እንዲያስደርጉ ጠይቋል።

አብያተ ክርስቲያንና ድርጅቶቻቸው ሁሉ በደቡብ አፍሪቃ ያለውን ተቀማጭ ገንዘብም ሆነ ማንኛውንም የደቡብ አፍሪቃ ዘረኛ መንግሥት መጠቀሚያ እንዳይሆን ርምጃ እንዲወስዱ ጉባኤው ከማስጠንቀቁም በላይ አብያተ ክርስቲያን አፓርታይድን ፣ የዘር ልዩነትንና የቅኝ አገዛዝን በሙሉ ልብና ኃይል መቃወም እንዳለባቸው በጥብቅ አስገንዝቧል ።

፪/ በጠቅላላው ስለ አፍሪቃ አህጉር ጸጥታ ፣

የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ በሕንድ ውቅያኖስ በኃያላን መንግሥታት የሚደረገውን የወታደርና የጦር ክምችት ጉዳይ መርምሯል ።

በተለይም በዲያጎ ጋሪሲያና በሪዩኒየን ለአፍሪቃ ሕዝብ ሰላም መቃብር የሚሆን የጦር ክምችት ጣቢያ መመሥረቱ ዓለምን የሚያሰጋ መሆኑን ጠቁሞ በዙሪያው በመገቢያየት የሚጠቀሙት ሕዝቦችና ዓሣ አጥማጆች በጦር መሣሪያ የውቅያኖሱ መንገድ የታጠረባቸው ስለ ሆነ በታላቅ ሥጋት የሚኖሩ መሆናቸውን ገልጿል ።

የደቡብ አፍሪቃ ዘረኛ መንግሥት የኒክሊየር መሣሪያ ባለቤት እንዲሆን መደረጉና በወታደር ኃይልም ከፍ እንዲል በምዕራባውያን መደገፉ ለዓለም ሰላም ጠንቅ ነው ፤ ለምሥራቅና ምዕራብ አፍሪቃ ህልውናም እጅግ በጣም አስጊ ነው ሲል ጉባኤው ስሞታውን አሰምቷል ። ጉባኤው በተለይ የተባበረው አሜሪካና ፈረንሳይ በሕንድ ውቅያኖስ የመሠረቱትን የጦር ክምችት እንዲያነሡ ጠይቋል ። ጉባኤው ከእስያ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ጋር የጋራ ችግር ስለ አለና ከሕንድ ውቅያኖስ ጀምሮ እስከ ፓስፊክ ውቅያኖስ ድረስ በአለው የጦርና የወታደር ክምችት ሕዝባችን ስለሚጠቃ ግንባር ፈጥረን ስለሰላም መታገል አለብን በማለት ያለውን የአንድነት ድምፅ አሰምቷል ።

፫/ በሰው ልጅ መብት ፣

የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ የአፍሪቃ መንግሥታት ድርጅት (O A U) የሰው ልጅ መብት ኮሚሽን ለማቋቋም አስቸኳይ ርምጃ እንዲወስድና በሕገ መዋቅር ውስጥም እንዲያስገባ አሳስቧል ።

፬/ የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ የወደፊት ሥራ፣

ጉባኤው ለወደፊቱ ሰላም ፣ ትክክለኛ ፍትሕና ነፃነት በጠቅላላው አፍሪቃና በመላው ዓለም እንዲሠፍኑ በይበልጥ እንዲደሚታገልና ለመሥራት የማያወላውል እቅድ እንዳለው ገልጿል። ለአፍሪቃ አኅጉር የጋራ ብልጽግና ትክክለኛ ፍትሕ ፣ ነፃነትና ሰላም ከሚታገሉ ተራማጅ ኃይላት ጋር ግንባር ፈጥሮ ድጋፍ እየሰጠ እንደሚታገልም አመልክቷል ።

የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ያለበት ታላቅ ኃላፊነት በየአገሩ የተቋቋሙትን ብሔራውያን የሰላም ኮሚቴዎችን ማጠናከር ፣ ከአፍሪቃ አብያተ ክርስቲያንና ልዩ ልዩ የአብያተ ክርስቲያን አንድነት ድርጅቶች ጋር አንድነትን ፈጥሮ መሥራት መሆኑን አምኖበታል ። በዚህሁሉ አጋጣሚ አብያተ ክርስቲያንና ልዩ ልዩ የክርስትና አንድነት ድርጅቶች የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤን ሙሉ ድጋፍ እንዲሰጡት በጥብቅ አሳስቧል ።

፭/ የሬዩኒየንና የሞሪሽየስ ክርስቲያኖች የሶሻሊስት ንቅናቄ ድርጅቶች የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ ዓባላት ሆነው ስለገቡ ጉባኤው ደስ ያለው መሆኑን በመግለጫው ገልጿል።

፮/ በ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በመስከረም ወር በመስቀል በዓል አካባቢ የዓለም ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ስብሰባ በአዲስ አበባ እንዲደረግ ተወስኗል ፤ ይህንኑም በጉብኝታቸው ወቅት የሰላም ልኡካኑ መግለጻቸው ይታወሳል ፤ በታናናሪቭ በተደረገውም ጉባኤ





www.ethiopianorthodox.org

የአፍሪቃ ክርስቲያኖች የሰላም ጉባኤ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ስብሰባ ከዓለም አቀፍ ጉባኤ ጋር በ፲፱፻፸፬ ዓ/ም በመስከረም ወር በአንድነት ቢፈጸም መልካም መሆኑ ታምኖበታል በማለት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመወከል በጉባኤው ላይ ተገኝተው ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊነትና ዝና እንዲሁም ስለ ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን አቋምና ዓላማ በማስረዳት በጠቅላላው አስፈላጊውን ተልእኮ ሁሉ አሟልተው የተመለሱት ሊቀ ካህናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ዋና ጸሓፊ ገልጸዋል ።

---

# በዓለ እስተርእዮ (ኤጲፋንያ)

## ምስክርነት የተሰጠበት ዕለት

እስተርእዮ ማለት መገለጽ ማለት ነው ይኸውም ጥልቅ ና ድንቅ ምሥጢር በአንደኛ ደረጃ የሥላሴ ፫ትነት ፤ በሁለተኛውም የአምላክ ሰው የሰው አምላክ መሆን ናቸው፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሁኖ ፴፫ ዓመት ከ፫ት ወር በዚህ ዓለም ኑሮ ሥራ ከሠራባቸው ዕለታት ፤ ከፍተኛ ምሥጢር የተገለጸበት ዕለት አንዱ ዋነኛው የጥምቀት ዕለት ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ድንቅ ምሥጢር ካሳየባቸው ቦታዎች አንዱ ዮርዳኖስ ነው ፤ በዕለቱ በሰጠው ምስክርነት ጌታ ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ ማቴዎስ ምዕራፍ ፫ ቁጥር ከ፲፭ እስከ ፲፯ የምወደው ልጄ ይህ ነው ያለ እግዚአብሔር አብ ሲሆን በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ሰው ሁኖ በጽንፈ ዮርዳኖስ ቁሞ የምወደው ልጄ ነው ተብሎ ምስክርነት የተነገረለት ደግሞ እግዚአብሔር ወልድ ሲሆን በአምሳለ ርግብ ወርዶ በወልድ ራስ ላይ ረቦ የታየው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ በዓሉ የጥምቀት በዓል ቢባልም እንደምሥጢሩ አመጣጥና አገላለጽ የሥላሴ በዓል መባል ይገባዋል ምክንያቱም አኮኑ ዝንቱ አብ ፈጠረከ ፤ ፈጠረከሂ ወገብረከ ። ለመሢ ሑ ለወልደ እግዚአብሔር መኑ ስሙ ፤ መንፈስ ወስደኒ ኀበ ርጊብ ወስፉህ መካን ፤ ተብሎ ስለ አብ ስለወልድ ስለመንፈስ ቅዱስ የተነገረው ትንቢት ምሳሌው በአማናዊነት የተገለጸበት ዕለት ስለሆነ የሥላሴ በዓል ነው ። ሁለተኛ ምስክር በማግስቱ ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስን ወደእርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሁኖአል ብዬ ስለእርሱ ያልሁት ይህ ነው መንፈስ ከሰማይ እንደርግብ ሁኖ ሲወርድ አየሁ በእርሱ ላይም ኖረ እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መስክሬአለሁ ዮሐንስ ምዕ ፩ ቁጥ ከ፳፱ እስከ ፴፭ ያለው ሲሆን ምስክሩ ዮሐንስ ክርስቶስን ብእሲ ብሎ በሰውነቱ የባሕርይ አምላክ የባሕርይ ልጅ መሆኑን ሲያስረዳ አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል ከእኔም በፊት ነበር ፤ ብሎ ቀዳማዊነቱን ደኃራዊነቱን አምላክ ወሰብእ መሆኑን ቅድመ ዓለም ከአብ ድኅረ ዓለም ከቅድስት ድንግል መወለዱን ሲያስረዳ እግዚአብሔር ወልድን በሰውነቱ የባሕርይ ልጅ አድርጎ ዮሐንስ መጥምቅ ብእሲ ዘሀሎ እምቅድሜየ ይመጽእ እምድኅሬየ ብሎ ምስክርነትን ስለሰጠ ይህ ዕለት ምሥጢራት የመነጩበትና የተገለጹበት ዕለት ስለሆነ ዘመነ እስተርእዮ ተባለ ሆኖም የባሕርይ አምላክነት ምስክርነት በዕለቱ ተሰጠ ለማስረጃም አምላካዊ ምሥጢር ታዩ ብለን የጥምቀቱን ምሥጢር ልናልፈው ስለማይገባ ወደ ጥምቀቱ ጉዳይ ገባ ብለን እንመልከት ። ጥምቀት ለአይሁድም ነበራቸው በዚያም ልማድ ለዮሐንስም ጥምቀት ነበረው ። ሆኖም ከሰውነታቸው ሰውነቱ እንዲበልጥ ከጥምቀታቸውም ጥምቀቱ ይበልጥ ነበር እርሱም ስለራሱ ጥምቀት እንዲህ እያለ ተናግሯል እኔስ ለንስሐ በውሀ አጠምቃችኋለሁ ጫማ ውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል ብሎ የራሱን ጥምቀት የንስሐ ጥምቀት ብሎ ጠርቶታል ጥምቀት ኃይል ብርታት ያገኘ ግን ጌታ በመጠመቁ ነው ዮርዳኖስ የሥላሴን ምሥጢር ለማሳወቅ እንደበቃ እኛም በመጠመቃችን ማኅደረ ሥሉስ ቅዱስ እንሆናለን የሥላሴን ምሥጢር ለመረዳት እንችላለን እንደ ዮሐንስ ም አባባል ጥምቀታችን የንስሐ መሆኑ ቀርቶ ልጅነትን የሚያሰጥ ጥምቀት ይሆናል ። ይኸውም ዮሐ በምዕራፍ ፫ ቁጥ ፭ እስከ ፮ ባለው እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃሃ ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ያለውና ቅ/ ጳውሎስም ለቲቶ በጻፈው መልእክቱ በምዕ ፫ ቁጥር ፭—፮ እንደምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በሙታደስ አዳነን ብሏል ። ይህ ከሆነ ጥምቀተ አይሁድም ሆነ ጥምቀተ ዮሐንስ በአዳም የሄደውንልጅነትእንዲመለስ ማድረግ አልቻሉም በጥምቀት ከሥላሴ ተወልዶ ልጅነት የተገኘ ግን ጌታ ጥምቀትን ተጠምቆ ለጥምቀት ኃይል ጽንዕ ከሰጠ በኋላ ነው ምንም ጥምቀቱ ለራሱ ረባው ጠቀመው ባይባልም እኛ ተጠምቀን ከሥላሴ ተወልደን ልጅነትን አግኝተን እንድንጠቀምበት ለጥምቀት ኃይል ጽንዕ ስለሰጠልን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸርነቱን በማሰብ በየዓመቱ በዓለ ጥምቀቱን እናከብራለን ያለጥምቀት መዳን የሌለ መሆኑን ሲያስረዳ በሲኦል ላሉ ነፍሳት ስንኳ ቀኝ እጁን ቢያሳያቸው ጥምቀት ሁኖአቸዋል ብሏል ወኮነቶሙ ፡ ጥምቀተ እደ የማኑ እንዲል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነትና ለጋስነት ለጥምቀት ኃይል ጽንዕ ሰጠ በማለት ብቻ ተነግሮ ሊበቃ አይችልም ይኸንንም ለመረዳት ቅዱስ ጳውሎስ ለሮም ሰዎች በጻፈው በምዕ ፭ ቁጥር ከ፲፪ እስከ ፲፯ ባለው ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት ፤ እንደዚሁ



ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቆጠርም በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሙተዋልና ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙ ዎች በዛ ይላል በአዳም የኃጢአት ተገዥነት ተጽፎ የነበረ የእዳ ደብዳቤን አጥፍቶና ፍቆ አዳም ዕፀ በለስን በልቶ በፍርድ ያስወሰዳትን ልጅነት ያስገኘበት ኃይል ቢኖር ዋነኛው ነገር ጥምቀት ነው ። ጥምቀትን በውሃ ላይ የመሠረተበት ምክንያትና ከዚያውም ላይ በዮርዳኖስ ያደረገበት ሌላ ባሕር ጠፍቶ ሳይሆን የተነገረው ትንቢት በአፈጻጸም ሥራ ላይ እንዲውል ብሎ ነው ይኸውም ባህር አየች ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ አንቺ ባሕር የሸሸሽ አንቺም ዮርዳኖር ወደ ኋላሽ የተመለስሽ ምን ሁናችኋል ከያዕቆብ አምላክ ፊት ከጌታ ፊት ምድር ተናወጠች መዝሙር ፻፲፫ ቁጥር ከ፫ እስከ ፰ የሚል ስላለ ቦታውም ዮርዳኖስ መጠመቂያውም ውሃ እንዲሆን የሆነ ከዚህ ትንቢት አነጋገር የተነሣመሆኑ ግልጽ ነው ፤ ከዚህም ሌላ ውድነት ባላቸው በማር ወይም በወተት ጥምቀትን አልመሠረተውም ሥጋውን ደሙን ከቡነርት ባላቸው በወርቅ በእንቁ እንዳልሰጠ ሰው ሁሉ ሊያገኘው በሚችል በስንዴ በወይን እንደሰጠ ጥምቀትንም ሁሉ ሊያገኘው በሚችል በውሃ ሰጥቷል ደግሞም ማር ወተት መልክዓ ሥጋ አያሳዩም ውሃ ግን እንደመስተዋት ያሳያል በጥምቀትም መልክዓ ነፍስ እንዲታይ ለማጠየቅ በውሃ ተጠመቀ ከዚህም ሌላ ማርናወተትተክል ያደርቃሉ እንጂ አያለመልሙም ውሃ ግን ተክል ያለመልማል በጥምቀትም ልምላሜ ነፍስ ይገኛልና ማርና ወተት ልብስ ያሳድፋሉ እንጂ አያነጹም ውሃ ልብስ ያነጻል በጥምቀትም ንጽሐ ነፍስ ይገኛልና ። ደግሞም ወእነዝኃከሙ በማይ ንጹሕ ወትነጽሑ እምርኩስክሙ ንጹሕ ውሃን እረጫችኋለሁ ንጹሐንም ትሆናላችሁ ያለውን ትንቢታዊ ቃል ለማጽደቅ በውሃ ተጠመቀ

## የጥምቀት ፍሬ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጥምቀት ኃይል ጽንዕ ሰጥቶ በአዳም በደል የሔደውን ልጅነት ለሰው ልጆች እንድትመለስ ያደረገበት የጥምቀት ፍሬ ምንድነው ቢባል ተጠምቆ ሳይውል ሳያድር ዕለቱን ገዳመ ቆሮንቶስ የመግባቱ ጉዳይ ነው ይኸውም እምነትም ሆነ ጥምቀት ለልጅነት ቢያበቃ ክብር ማግኘት በሥራም ጭምር መሆኑን ለማስረዳት የጥምቀት ፍሬ የሆነውን የትሩፋት መሠረት ጾምን ሕግ አድርጎ ለጥምቀት ኃይል ጽንዕ እንደሰጠ ለጾምም ኃይል ጽንዕ ሰጥቶ የዚህን ዓለም የኃጢአት አበጋዝ ዲያብሎስን ድል ነስቶ ጽንዑ እስመ አነ ሞዕክዎ ለዓለም በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ ዮሐ ምዕ ፲፮ ቁጥ ፴፫ ብሎ የተስፋ ቃልን ያበሠረበትየጥምቀት ፍሬ ጾም መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል ሰውን ማመኑና መጠመቁ ብቻ ለክብር የሚያበቃው ቢሆን ኑሮ ጌታ ተጠምቆ ዕለቱን ገዳመ ቆሮንቶስ ባልገባ ነበር ምንም እክብር አይል ክቡር እጸድቅ አይል ጻድቅ ሲሆን ሥራውን ሁሉ ሠርቶ ሥሩ በማለቱ ትሩፋትን ዋጋ የምታሰጥ ለማድረግ ነው እንጂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሁኖ ሥጋን ተውህዶ የሠራው ሥራ ሁሉ ለካሣ ለኛ ቤዛ ለመሆን ሰይጣንን በፈሊጥ አቅርቦ ሲቀርብ ድል ለመንሣት ያደረገው መሆኑን መጻሕፍት አስረድተዋል አኮ ፈቂዶ ለተጠምቆ አላ ከመየሃበነ ሱታፌ ንጽሕ መጠመቁ ሽቶት የሚያስፈልገው ሁኖ አይደለም ። በመጠመቁ ለእኛ ሀብተ ንጽሕናን ይሰጠን ዘንድ ነው እንጂ ብለው ልጅነትንም ማግኘት ብቻ ለክብር የሚያበቃ ቢሆን ኑሮ ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው ቃለ መልእክት ምዕ ፩ ቁጥር ከ፳፱ — ፴ባለው ይህ ስለክርስቶስ ተሰጥቷችኋልና ስለእርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም በማለት የእምነት የጥምቀት ፍሬው የትሩፋት ሥራ መሆኑን አስረድቷል ። ትሩፋትም ማለት ጾም ጸሎት ምጽዋትና ሌሎችም የምግባረ ሠናይ ሥራዎች ሁሉ ናቸው ።

መልአከ ፀሐይ ታፈሰ ደሳለኝ
የየካ ደብረ ማህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ።



www.ethiopianorthodox.org

መጀመሪያ በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ፩ኛ ዮሐ ፩፣ ፩—፬ ተወግዘዋል ፣ ከዚያም የሐዋርያት ተከታዮች ፣ ቅዱስ እግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ፤ ሄሬኔዎስ ኤጲስ ዘኢዮም (ዘሊኦን) ቀሌምንጦስ ዘሮም ፤ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ናእንደዚሁም ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አባቶች አውግዘዋቸዋል ። በተጨማሪም ለብዙዎች ሰዎች አስቸጋሪ ሆነው የተገኙትን የቅዱሳት መጻሕፍትን ኃይለ ቃላት አሰጥፍተውና አመሥጥረው በመተርጎም የመለኮትንና የትስብእትን ፍጹምተዋሕዶ በሚገባ በመረዳትና በማስረዳት ብዙ መጻሕፍትን ጽፈዋል በተለይም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመከራው (ከመሰቀሉ) በፊት የፈራው ፍርሃትና የታወከው መታወክ እማናዊ መሆኑን አበው ቅዱሳን በጽሑፋቸው አረጋግጠዋል ።

ይኸውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የፈራው ፤

፩ኛ/ ፍጹም የሆነ ባሕርየ ትስብእትን ያለመለወጥ መዋሐዱን ለማረጋገጥ ፣

፪ኛ/ የእኛን ፍርሃትና ጭንቀት ከኛ ለማስወገድ

፫ኛ/ አስፈርቶንና አስደንግጦን የነበረውን ዲያብሎስን (ሰይጣንን) ለማቅረብና ለማሠርነው በማለት አስተምረዋል። ለምሳሌ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ «አምላኪየ አምላኪየ ለምን ትውከኝ» የሚለውን ኃይለ ቃል ሲያብራራ «ወሶበ ተሳተፈ መድኃኒነ ሥጋ ወደመ ከማነ ኖለቈ ርእሶ ከመ አሐዱ እምኔነ ለነ እለ ኀደገነ እግዚአብሔር እምኔሁ በዐሊዎትነኪያሁ ይቤ ዘንተ ቃለ በእንተ ሀላዌነ አምላኪየ አምላኪየ ለምንት ኃደገነ «ከመ ይሥዓር በቃሉ መርገመ ዘረከበነ በበቀል» መድኃኒታችን እንደ እኛ ነፍስንና ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ተለይተን የነበርን እኛ እንደ አንዱ ራሱን ቈጠረና በዚህ አነጋገር በአዳም ሕግ ማፍረስ ምክንያት ያገኘንን ፍዳ ያጠፋ ዘንድ ያን ጊዜ ስለ ባሕርያችን ይህንን ቃል ተናገረ» በማለት ተናግሯል ሃይማኖተ አበው ገጽ ፫፪፭፫ ፣

የአርዮሳውያን ዋና ደመኛ የነበረው ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያም ይህንን ሲተረጉም እንዲህ ብሏል ። «ወበብሂሎቱስ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላኬ ለምንት ኀደገኒ እሙነ ያጤይቅ ዘንተ ቃለ በእንቲአነ» የእኛን ሥጋ ያለ መለወጥ መዋሐዱን ያረጋግጣል እንደዚሁም ይህንን ያለው ስለ እኛ ነው» ብሏል አትናቴዎስ ፮ኛ መጽሐፍ ገጽ ፵፩ ፣ ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያም (አኮ ዘይቤ እግዚእነ አምላኬ ለምንት ኀደገኒ በእንተ ርእሱ እስመ ለሊሁ ውእቱ እግዚአብሔር አላ ይቤ ዘንተ በእንቲአነ ለእለ ኀደገነ እግዚአብሔር ውስተ ፍርሃተ ሞት» ጌታችን አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ ያለው ስለራሱ አይደለም እሱእራሱ እግዚአብሔር ነውና ነገር ግን ይህንን ያለው እግዚአብሔር በሞት ፍርሃት ላይ ስለተወን ስለኛ ነው ፣ እንጂ ሲል አስረድቷል ሳዊሮስ ፈላሊስ ገጽ ፪፻፲፩) በዚሁ መሠረት ዳግመኛም ስለ ክርስቶስ መከራና ፍርሃት ሲተረጕም «ሶበሰ ኢፈርሃ እምሃለወ ፍርሃት ለዝሉፋላዕለ ሀላዌ ዕጓለ እመሕያው ሶበሰ ኢሐመኢምኢረከቡ ግዕዛነ ዕጓለ እመሕያው እምነ ሕማም ወትካዝ ፤ ሶበሰ ኢትሀውከ እምኢሰሰሉ ሁከታት እምኔነ «ባይፈራስ ኖሮ ፍርሃት በሰው ባሕርይ ላይ ለዘለዓለሙ ጸንቶ በኖረ ነበር ፤ ባይታመምስ ኖሮ ሰዎች ከሰማይያዊ ሐዘን ከመተከዝ ነፃ መሆን ባልቻሉም ነበር ፣ ባያዘንም ኖሮ ኃዘናት ከእኛ ባልራቁም ነበር» በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ፍርሃትና ኃዘናትን ለማስወገድ በሰውነቱ እንደፈራና እንደ አዘነ ፣ ማዘኑና መተከዙ በምትሀት እንዳይደለ አስረድቷል (ሃይማኖተ አበው ገጽ ፫፻፳፭)

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፣ ቅዱስ ቴዎድሮስ ዘእንቆራ ፣ ቅዱስ ፕሮክሊስ (ኤራቅሊስ) ዘቁስጥንጥንያ እምፍሉስ ዘኤቆና «አባ አሕልፋ ለዛቲ ጽዋዕ» የሚለውን ኃይለ ቃል ሲተረጉሙ «ወቢሃሎቱሰ አባ እህልፋ ለዛቲ ጽዋዐ ሞት» ኮነ ከመ ይሂጦ ወይትመየኖ ለሰይጣን እንዘ ያርኢ ትስብእቱ በከመ ያርእዮ ለዓሣ ላዕፈ ወድዮሙ ዲበ መጣቅን በአንቀሩ ወሶበ ተፋአማ እንዘ የኀሥሥ ሲሳየ ይእሀዞ መጣቅን በአንቃሩ ወከመዝ ሰይጣንኒ ሶበ ተፍእማ ለላዕፈ ሥጋሁ ለክርስቶስ ዘብሐ ሰይፈ መለኮት ጉርዔሁ» ጌታችን አባ አሕልፋ ለዛቲ ፅዋዕ ማለቱ ሰይጣንን አታልሎ ለማቅረብ ነው በመቃጥን (ወጥመድ) ላይ ቁራጭ ሥጋ አድርገው ለመብላት የሚመጣው ዓሣ በወጥመዱ ጉሮሮው (ላንቃው እንደሚያዝ ሁሉ ሰይጣንንም የክርስቶስን ሥጋ ለመያዝ በቀረበ ጊዜ በመለኮቱ ተያዘ ታረደ ማለት ተሻረ በማለት አስተምረዋል ። በዚህ ዓይነት ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጌታ የፈራውና ያዘነው ለአጽንኦተ ትህብእት (ሥጋዊውን ለማረጋገጥ) ፍጹም ሰው መሆኑን ለማረጋገጥና እንዲሁም ለአቅርቦተ ሰይጣን መሆኑን በስፊው አስረድቷል ።



www.ethiopianorthodox.org